

የሐዋርያው የጳውሎስ መልእክት

# ወደ ሮሜ ሰዎች

ክፍል ሁለት

ማስጠኛ

# ማውጫ


| | |
|---|---|
| ክፍል ዘጠኝ | 5 |
| ክፍል አስር | 12 |
| ክፍል አስራ አንድ | 17 |
| ክፍል አስራ ሁለት | 22 |
| ክፍል አስራ ሦስት | 28 |
| ክፍል አስራ አራት | 34 |
| ክፍል አስራ ዓምስት | 41 |
| ክፍል አስራ ስድስት | 46 |




## መግቢያ

በክፍል አንድ ጥናታችን እንደተነጋገርነው፥ የሮሜ መልእክት ዋና አሳብ፥ ምዕራፍ 1፥2-6 በምናገኘው “ወንጌል” በሚለው መሪ ቃል የተጠቃለለው አሳብ ሊሆን ይችላል።

ሮሜ 1፥2-6 ላይ ጳውሎስ ስለ ወንጌል ይዘት በሚገልጽበት ጊዜ፡-

1. ወንጌል የተስፋ ቃሉ ፍጻሜ ስለመሆኑ፣ (ቁ.2)
2. ወንጌል ስለሆነው አካል(ስለክርስቶስ) ማንነት (3)፣
3. ወንጌል ስለሚያስገኘው ነገር (ቁ.5)እና
4. ስለ ወንጌል አላማ (ቁ.6) አብራርቷል።

ሐዋርያው ጳውሎስ መልእክቱን ለመጻፍ የተጠቀመበት ዘይቤ ልክ በችሎት ቀርቦ እንደሚሟገት አይነት ጥያቄ በማቅረብ ሲሆን፥ መልእክቱ በሁለት መሠረታዊ መደቦች ተከፍሎ መታየት ይችላል።

1. የመጀመሪያዎቹ አሥራ አንድ ምዕራፎች የክርስትናን ዶክትሪን (ትምሕርት / አስተምህሮ) ያካተቱ ሲሆን፣
2. የተቀሩት አምስት ምዕራፎች ደግሞ የክርስትናን ዶክትሪን (ትምህርት) ተግባራዊ ትንታኔዎች የሚያካትቱ ናቸው።

## የሮሜ መልእክት ማውጫ

I. መግቢያ (1፥1-17)
   ሀ. ጳውሎስን በተመለከተ (1-5)
   ለ. በሮም ያሉትን ወገኖች በተመለከተ (6-15)
   ሐ. ወንጌልን በተመለከተ (16-17)

II. ጽድቅ በእምነት (1፥18-11፥36)
   ሀ. ኃጢአት - የደኅንነት አስፈላጊነት
      1. ለአሕዛብ (1፥18-2፥16)
      2. ለአይሁድ (2፥17-3፥8)
      3. ለዓለም ሁሉ(3፥9-20)

   ለ. ጽድቅ በእምነት - የደኅንነት መሰፈርት
      1. በእምነት የሚሆን የእግዚአብሔር ጽድቅ (3፥21-31)
      2. የአብርሃም ምሳሌነት (4፥1-25)

ሐ. ነጻነት- የደኅንነት ውጤት

1. ከቁጣ ነጻ (5፥1-21)
2. ከኃጢአት ነጻ (6፥1-23)
3. ከሕግ ነጻ (7፥1-25)
4. ከሞት ነጻ (8፥1-39)

መ. አይሁድና አሕዛብ- የደኅንነት ክልል

III. እግዚአብሔር የሚያምኑትን ለማዳን መረጠ (9፥1-33)

1. እሥራኤል በራሷ ጽድቅ ለመታመን መረጠች (10፥1-21)
2. አይሁድም ሆኑ አሕዛብ በእምነት ደኅንነት ማግኘት ይችላሉ (11፥1-36)

IV. የተለወጠ ሕይወት (12፥1-15፥13)

ሀ. አጠቃላይ ምግባርን በተመለከተ (12፥1-21)

ለ. የሕዝብ ባለስልጣናትን በተመለከተ (13፥1-7)

ሐ. ሌላን ሰው በተመለከተ (13:8-14)

መ. ደካማ ወንድምን በተመለከተ (14፥1-15፥13)

V. መደምደሚያ አሳቦችና ቡራኬ (15፥14-16፥27)



# ክፍል ዘጠኝ

## ኃጢአት - የደህንነት አስፈላጊነት
ለአይሁድ (2፥17-3፥8)

አንተ ግን አይሁዳዊ ብትባል በሕግም ብትደገፍ በእግዚአብሔርም ብትመካ፥ ፈቃዱንም ብታውቅ ከሕግም ተምረህ የሚሻለውን ፈትነህ ብትወድ፤ በሕግም የእውቀትና የእውነት መልክ ስላለህ፥ የዕውሮች መሪ፥ በጨለማም ላሉ ብርሃን፥ የሰነፎችም አስተማሪ፥ የሕፃናትም መምህር እንደ ሆንህ በራስህ ብትታመን፤ እንግዲህ አንተ ሌላውን የምታስተምር ራስህን አታስተምርምን? አትስረቅ ብለህ የምትሰብክ ትሰርቃለህን? አታመንዝር የምትል ታመነዝራለህን? ጣዖትን የምትጸየፍ ቤተ መቅደስን ትዘርፋለህን? በሕግ የምትመካ ሕግን በመተላለፍ እግዚአብሔርን ታሳፍራለህን? በእናንተ ሰበብ የእግዚአብሔር ስም በአሕዛብ መካከል ይሰደባልና ተብሎ እንደ ተጻፈ።  ሕግን ብታደርግ መገረዝስ ይጠቅማል፤ ሕግን ተላላፊ ብትሆን ግን መገረዝህ አለ መገረዝ ሆኖአል። እንግዲህ ያልተገረዘ ሰው የሕግን ሥርዓት ቢጠብቅ አለመገረዙ እንደ መገረዝ ሆኖ አይቈጠርለትምን? ከፍጥረቱም ያልተገረዘ ሕግን የሚፈጽም ሰው የሕግ መጽሐፍና መገረዝ ሳለህ ሕግን በምትተላለፈው በአንተ ይፈርድብሃል። በግልጥ አይሁዳዊ የሆን አይሁዳዊ አይደለምና፥ በግልጥ በሥጋ የሚደረግ መገረዝም መገረዝ አይደለምና፤ ዳሩ ግን በስውር አይሁዳዊ የሆነ አይሁዳዊ ነው፥ መገረዝም በመንፈስ የሚደረግ የልብ መገረዝ ነው እንጂ በመጽሐፍ አይደለም፤ የእርሱ ምሥጋና ከእግዚአብሔር ነው እንጂ ከሰው አይደለም።

በሮሜ መልዕክት ክፍል አንድ ጥናት ላይ፥ ጳውሎስ ራሱን በተመለከተ (1፥1-5)፣ በሮም ያሉትን ወገኖች በተመለከተ ( 1፥6-15)፣ ወንጌልን በተመለከተና( 1፥16-17) ጽድቅን በተመለከተ፥ ስለ አሕዛብ የጻፈውን ተመልክተናል (1፥18- 2፥16)።
በዚህ ጥናት ደግሞ ባለፈው ካቆምንበት በመቀጠል፥ የተወሰኑ ክፍሎችን በዝርዝር ለመመልከት እንሞክራለን።

ጳውሎስ የሮሜ መልዕክቱን በጻፈበት ጊዜ ሮም ከፍተኛ ብልጽግና ላይ ብትገኝም እንኳ፥ የግብረገብ አዘቅት ውስጥ ተዘፍቃ ነበር ፤ ከዚህ ቀደም ባልታየ መጠን ፍቺ በጣም ተንሰራፍቶ ነበር፤ ጉቦና ወንጀል በከፍተኛ ደረጃ ተስፋፍቶ ነበር፤ ነገሥታቱና ተራው ኅብረተሰብ በግብረ ሰዶማዊነት ተጥለቅልቆ ነበር፤ አመጻም በዝቶ ነበር። ስለዚህ ጳውሎስ በሮሜ 1፥28 ላይ ፥

"እግዚአብሔርን ለማወቅ ባልወደዱት መጠን እግዚአብሔር የማይገባውን ያደርጉ ዘንድ ለማይረባ አእምሮ አሳልፎ ሰጣቸው።" ማለቱ ፥ ይታይ ከነበረው ሁኔታ አኳያ ተገቢ ነበር ማለት ይቻላል።

ሆኖም ግን፥ ጳውሎስ ወደ ዚህች ለማይረባ አእምሮ ታልፈው የተሰጡ ሕዝቦች ወዳሉባት ከተማ ለመሄድ ከፍተኛ ፍላጎት ነበረው። ምክንያቱም በሮሜ 1፥16 እንደ ገለጸው፥ "ወንጌል ... ለሚያምኑ ሁሉ የእግዚአብሔር ኃይል ለማዳን መሆኑን ተገንዝቧል። ስለዚህ አሕዛብ በወንጌሉ ኃይል እንዲለወጡ ይፈልጋል።

በተጨማሪ፥ አይሁድም እንዲሁ በእምነት የሆነውን ጸጋ በመቀበል በክርስቶስ ኢየሱስ አዲስ ወደ ሆነ ሕይወት እንዲገቡ ይፈልጋል። እንዲያውም በዚህ በሮሜ 2፥18-29፥ ጳውሎስ የሚያተኩረው በተለይ በአይሁድ ህብረተሰብ ላይ ነው።

ምንም እንኳ አይሁድ ከእግዚአብሔር የተሰጠ ሕግ ቢኖራቸውም ወይም ከአብርሃም የዘር ግንድ በመምጣታቸው በእግዚአብሔር ፊት የተለየ ስፍራ እንዳላቸው ቢተማመኑም፥ እነርሱም እንደ አሕዛብ በወንጌሉ ኃይል መለወጥ እንዳለባቸው ጳውሎስ በዚህ የመልእክቱ ክፍል ያስገነዝባል።

1. በሮሜ 2፥17-21 መሠረት አይሁድ ስለራሳቸው ያላቸው ወይም ሌሎች ኅብረተሰቦች ስለ አይሁድ ሊኖራቸው የሚችለው አመለካከት ምን ሊሆን እንደሚችል ጠቅሷል?

አይሁድ ራሳቸውን፥

- ከዘርና ከነገድ ሁሉ የተሻሉና ምርጥ የሆኑ ዘሮች አርገው ይመለከቱ ነበር፣
- የሙሴ ሕግ ስላላቸው ከመኩራራት ባሻገር እራሳቸውን፥ መሪ፣ በጨለማ ላሉ ብርሃን፣ መካሪና፣ አስተማሪ አርገው ይመለከቱ ነበር።
- ጣዖታትን ሳይሆን እውነተኛውን አንድ አምላክ የሚያመልኩ አድርገው ይመለከቱ ነበር። ስለዚህ በትክክለኛ ሁኔታ ውስጥ ነን ብለው ይተማመኑ ነበር።

2. ጳውሎስ እንደገለጸው፥ አይሁድ ራሳቸውን የሚያዩበት አመለካከት በዚህ ዘመን ያለችውን ቤተ ክርስቲያን አባላትም ሊገልጽ ይችላል ብለው ያስባሉ? ለምን? (ለዚህ መልስ የሚሰጡት ምናልባት የግል አመለካከትዎ ሊሆን ስለሚችል የሌላውን አመለካከት የተሳሳተ ነው በማለት መቃወም አይኖርቦትም።)



3. በሮሜ 2፥ 17-21 እንደተጠቀሰው፥ አይሁድ መባል፣ በሕግ መደገፍ፣ በእግዚአብሔር መመካት፣ ፈቃዱን (የእግዚአብሔርን ፈቃድ) ማወቅ ፣ የሚሻለውን ፈትኖ መውደድ፣ በሕግ የእውቀትና የእውነት መልክ መያዝ፥ የዕውሮች መሪ፣ በጨለማ ላሉ ብርሃን፣ የሰነፎች አስተማሪ፣ የሕጻናት መምህር መሆንና በራስ መተማመን፣ እንደመጥፎ የሚታዩ ነገሮች ናቸው? ለምን? ( በእያንዳንዱ ሐሳብ ላይ ያለዎትን አስተያየት ያካፍሉ።)

- አይሁዳዊ ብትባል፡- ይህ ስያሜ ለእግዚአብሔር የተለየ ሕዝብ ወይም አገር ውስጥ ብሔርተኛ ወይም ዜጋ መሆንን የሚገልጽ ነው። ታዲያ ይህንን ስያሜ የያዘ የተለየ ክብርና ኩራት ይሰማው ነበር።
- በሕግ ብትደገፍ፥ የብሉይ ኪዳን ሕግ ላይ መደገፍን የሚገልጽ ነው።
- በእግዚአብሔርም ብትመካ፡- በዚህ ክፍል መመካት የሚለው ቃል፥ መፎተትን ወይም መዘባነንን የሚገልጽ ነው። አይሁድ፥ እግዚአብሔር ከእነርሱ ጋር እንዳለ ያውቃሉ። ስለዚህ በአሕዛብ ፊት ይመጻደቃሉ፣ እግዚአብሔር የእነርሱ እንደሆነ አርገው ሌላውን በማጣጣል ይዘባነናሉ።
- ፈቃዱንም ብታውቅ፡- በዚህ ክፍል ጳውሎስ በቀላሉ ፈቃዱን ብታውቅ ብሎ ነው የገለጸው እንጂ ለፈቃዱ መገዛታቸውን አይገልጽም።
- የሚሻለውን ፈትነህ ብትወድ፡- በዚህ ክፍል ብትወድ የሚለው ቃል 'dokimazō' የሚለውን የግሪክ ቃል የሚተካ ነው። ይህ የግሪክ ቃል ታድያ፥ ነገርን ፈትኖ ትክክለኛነቱን ማረጋገጥን የሚገልጽ ነው። ባብዛኛው የሕግ መምህራን በዚህ ጉዳይ የተካኑ ነበሩ።
- በሕግ የእውቀትና የእውነት መልክ በመያዝ፥ የዕውሮች መሪ፣ በጨለማ ላሉ ብርሃን፣ የሰነፎች አስተማሪ፣ የሕጻናት መምህር መሆንና በራስ መተማመን፥ አይሁድ ወደ ምኩራብ በመሄድ ሕግን እንዲያጠኑ ይደረግ ስለነበር ባብዛኞቹ አይሁድ ሕግን አብጠርጥረው ያውቃሉ ብሎ ማሰብ ይቻላል።ስለዚህ ራሳቸውን አዋቂና የተሻሉ አርገው የመመልከታቸውን ጉዳይ የሚገልጽ አባባል ነው።

4. ጳውሎስ የብሉይ ኪዳንን ሕግ በመጠበቅ ወይም በማክረር የሚታወቁትን አይሁድን መንቀፉ፥ የብሉይ ኪዳንን ሕግ ማቃለሉ ነው እንዴ? ለመሆኑ የብሉይ ኪዳን ሕግ ሚና ምን ይመስሎታል? ታዲያ (ከሕግ ጋር በተያያዘ) የአይሁድ ችግር ምንድን ነው?

የብሉይ ኪዳንን ተግባር በአራት ከፍለን ልናስቀምጠው እንችላለን።

1. የእስራኤላውያንን አለመታዘዝ እርቃን ያወጣል (አጥርቶ ያሳያል)

2. የሰውን ኃጢአተኝነት ይገልጣል

3. የእግዚአብሔርን ቅድስና ይገልጣል

4. ወደ ኢየሱስ ይጠቁማል (ሊመጣ ላለው መሲህ ጥላ ነው።)

አይሁድ ሊጠቀሙበት የሚችሉት ሕግ ቢኖራቸውም እንኳ ሊጠቀሙበት አልቻሉም ነበር። ሕግ የተሰጣቸው ወይም የእግዚአብሔርን ቃል በማወቅ ቀዳሚ የነበሩ ቢሆንም እንኳ፥ የቃሉን ኃይል ክደው በከንቱ ልምምድና ሥርዓት ተይዘው ነበር። ስለዚህ የእግዚአብሔር ክብር በሕይወታቸው እንደሚገባው ሊገለጥ አልቻለም። (2ኛ ጢሞቴዎስ 3፥5)

ምንም እንኳ አይሁድ፥ ጳውሎስ በሮሜ 2፥17-21 በዘረዘራቸው ምክንያቶች የተነሳ በእግዚአብሔር ፊት ከፍተኛ ቦታ እንዳላቸው ቢመስላቸውም፥ እውነታው ግን ከዚያ የተለየ ነበር። እነርሱ ስለራሳቸው የሚያስቡትና እግዚአብሔር ስለ እነርሱ የሚያስበው ለየቅል ነበር። ጳውሎስ የሚያሳስባቸው ይህንኑ ነው። አይሁድ ስለራሳቸው እንደሚያስቡት ሳይሆን የሚጠበቅባቸውን መሆን ያቃታቸው መሆኑን ያስገነዝባቸዋል።

ወገኖች፥ ዛሬም እኛ እንዲሁ በግምት ወይም በራሳችን አይን መልካም እንደመሰለን ዝም ብለን እየተጓዝን ሊሆን ይችላል። ስለዚህ ዝም ብለን ከመንጎድ ይልቅ፥ ቆም ብለን፥ “እግዚአብሔር አሁን ስላለንበት ሁኔታ ምን ይል ይሆን?” በማለት ድምጹን በመንፈሱ በኩል በቃሉ እንዲያሰማን መፈለግ አለብን።

ጌታ ኢየሱስ እንደተናገረው የእረኛችንን ድምጽ አጥርተን በመስማት የምንከተል በጎች መሆን የግድ አስፈላጊ ነው። በየዕለቱ እርሱን እየሰማን የምንከተለው ከሆነ ብቻ ነው በጽድቅ መንገድ ልንገሰግስ የምንችለው።



ለዛሬይቱ ቤተ ክርስቲያን ሕግን ሳይሆን ክርስቶስ ራሱን ሰጥቷታል፣ “ የእግዚአብሔር ሰው ፍጹምና ለበጎ ሥራ ሁሉ የተዘጋጀ ይሆን ዘንድ፥ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ... ” ተሰጥቷታል፣ ረዳት የሚሆን መንፈስ ቅዱስም ተሰጥቷታል። ጥያቄው ታዲያ ይህን እየተጠቀመችበት ነው? ወይስ የተሰጣትን መልካም ስጦታ እንዲሁ በከንቱ እየተኩራራችበት ነው?

5. ከሚታየውና ከሚሰማው አኳያ እርስዎ ምን ይመስሎታል?

ከቴክኖሎጂ፣ ከሕንፃ ግንባታ፣ ከወግና ሥርዓት እንዲሁም ከማኅበረሰብ ቁጥር ብዛት አኳያ ስንመለከት፥ ዛሬ ቤተ ክርስቲያን በጣም ከፍተኛ በሆነ ርቀት የተጓዘችበት ጊዜ ላይ ነው ያለነው። በእርግጥ ቤተክርስቲያን በነዚህ ነገሮች ማደጓና እርቃ መጓዟ በጣም ጥሩ ነው! ሆኖም ግን፥ ከመካከሏ ምናልባት፥ “ስድሳ ምዕራፍ ወደ ሚርቅ ወደ ኤማሁስ” እንደተጓዙት ደቀ መዛሙርት የራስን አጀንዳ በመያዝ ወደ መሰላቸው የሚጓዙና ክርስቶስ በሚፈልጋቸው ቦታና ሁኔታ ላይ የሌሉ ብዙዎች ሊኖሩ ይችላሉ። በእንዲህ ሁኔታ የምንገኝ ካለን እንደ ኤማሁስ መንገደኞች ጌታ ለኛም ይድረስልንና ወደ መስመር ያስገባን።

ወገኖች፥ በዚህ በሰሜን አሜሪካ እንደሚታየው ቤተ ክርስቲያን በጣም ተራቃለች፣ ብዙ ትላልቅ ቤተ ክርስቲያኖች አሉ፣ አምልኮው በጣም ያደገና የደመቀ ነው፣ በተለያዩ የመገናኛ ዘርፎች የሚሰራጩ ግሩም የሆኑ መንፈሳዊ ፕሮግራሞች እየተካሄዱ ነው ከነዚህም መካከል አንዳንዱ በጣም ጊዜውን ከመምሰሉ የተነሳ አለማዊ ወይ መንፈሳዊ መሆኑን ለመለየት ትንሽ አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል።

ምናልባት እኛም የኢትዮጵያ ክርስቲያን ማህበረሰብ፥ ራሳችንን ብቻ ሳይሆን ክርስትናችንንም አሜሪካዊ በማድረግ ቤተ ክርስቲያናችንንና ክርስትናችንን መንፈሳዊ ሳይሆን የምንኖርበትን አካባቢና ጊዜ እንዲመስል አርገነው ሊሆን ይችላል።

ወገኖች፥ በምናየው ውጫዊ ነገር እንዳንታለል መጠንቀቅ ያስፈልገናል። ላዩ ወይም ሽፋኑ የራሰ ነገር ሁሉ ከውስጡ ሞልቶ የሚፈስ የሕይወት ውሃ አለው ማለት አይቻልም። ምክንያቱም ውሃ ውስጥ ዝም ብሎ በመነከር ውጪው ረጥቦ ውስጡ ደረቅ መሆን ይቻላልና ነው።

ስለዚህ ወገኖች፣ እያንዳንዳችን በእግዚአብሔር ፊት ልባችንን እየፈተሽንና እያስፈተሽን በየዕለቱ ለመታደስ መዘርጋት አለብን። በልማዳዊና በሚመስል ሕይወት ተሞልቶ ከመኩራራት ይልቅ እውነተኛና የታደሰ መንፈሳዊ ሕይወት የሚሰጠውን የእግዚአብሔርን ጸጋ በትሕትና መፈለግ ይገባናል።

"በተነ፥ ለምስኪኖች ሰጠ፥ ጽድቁ ለዘላለም ይኖራል።ተብሎ እንደ ተጻፈ፥ እግዚአብሔር፥ ሁልጊዜ በነገር ሁሉ ብቃትን ሁሉ አግኝታችሁ ለበጎ ሥራ ሁሉ ትበዙ ዘንድ፥ ጸጋን ሁሉ ሊያበዛላችሁ ይችላል።"
(2ኛ ቆሮንቶስ 9፥8-9)

"ነገር ግን ጸጋን አብልጦ ይሰጣል፤ ስለዚህ፦ እግዚአብሔር ትዕቢተኞችን ይቃወማል፥ ለትሑታን ግን ጸጋን ይሰጣል ይላል።"
(የያዕቆብ መልእክት 4፥6)

6. ጳውሎስ በገለጸው መሠረት፥ አይሁድ እንደሚገምቱት በሚያኩራሩና በሚያመጻድቅ ሁኔታ ላይ ያለመገኘታቸው ማረጋገጫ ምንድን ነው? (ሮሜ 2፥21-24)

- እንደሚያስተምሩት አይኖሩም :- ሌሎችን ለማስተማር ይሻሉ። ነገር ግን የሚያስተምሩትን ለራሳቸው አይኖሩትም።
- ሕግን ይተላለፋሉ፡- በሌሎች ላይ የሚጭኑትን ሕግ ራሳቸው አይፈጽሙትም፥ ስለዚህ "የእኔ ናቸው!" ብሎ በስሙ የለያቸውን እግዚአብሔርን ያሳፍራሉ።
- ድርጊታቸውና ሁኔታቸው የእግዚአብሔርን ስም ያሰድባል፡- በዚህ ክፍል ስድብ የሚለው በተለይ ከፍተኛ የሆነን ክስ ለማመልከት እንደሆነ ይነገራል። ስለዚህ አይሁድ በሚፈጽሙት ስህተቶች አሕዛብ እግዚአብሔርን እንዲከሱ ወይም "አምላካቸው እንዲህ ያደርጋል እንዴ?" እያሉ በእግዚአብሔር ላይ መሳለቃቸውን የሚገልጽ ነው።

ዛሬም እኛ ክርስቲያኖች በእግዚአብሔር፣ በክርስቶስ፣ በመስቀሉ፣ በመከራችን፣ በድካማችን መመካት የተገባን ነን። ነገር ግን፥ ትምክህታችን ከንቱ አለመሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል

7. በሮሜ 2፥21-23 እና በማቴዎስ 7፥16 መሠረት በክርስቶስ ያለን ትምክህት ከንቱ አለመሆኑ ማረጋገጫው ምንድን ነው?

8. በሮሜ 2፥25-26 ጳውሎስ፥ ሊገልጽ የፈለገው አሳብ ምንድን ነው? በዚህ ክፍል ምን ለማለት የፈለገ ይመስልዎታል? በፊልጵስዩስ 3፥3 ደግሞ፥ የአዲስ ኪዳን ቅዱሳን



የተገረዝን መሆናችንን ይገልጻል። በዚህ መሠረት ጳውሎስ በሮሜ 2፥25-26 ስለ አይሁድ የተናገረው ለኛ ምን ያስተምረናል?

ጳውሎስ በሮሜ 2፥25 የሚገልጸው፥ መገረዝ የሚጠቅመው ሕጉ እስከተጠበቀ ድረስ ብቻ ነው። በቁጥር 26 ላይ ደግሞ እኛም በክርስቶስ እንደገና ስንወለድ፥ ጌታ በመንፈሱ የልባችንን ሸለፈት መግረዙን ይጠቁማል (ቆላስይስ 2፥11) ። ስለዚህ እኛም ክርስትናችን በስም ብቻ ሳይሆን በተግባር የተገለጠ መሆን አለበት።

በሮሜ 2፥27 ጳውሎስ የመታዘዝንና ያለመታዘዝን ግልጽ ውጤት ካስቀመጠ በኋላ በቁጥር 28-29 ላይ እውነተኛ ግዝረት ውጫዊና ሥጋዊ ሳይሆን በመንፈስ የልብ ግዝረት ሲኖር የሚፈጸም መንፈሳዊ ድርጊት መሆኑን ያስገነዝባል።

9. ከዛሬው ጥናት ምን ተገነዘቡ? በዚህ ጉዳይ መውሰድ የሚገባዎት እርምጃ ካለ ምንድን ነው?

ወገኖች፥ ዛሬ ተግባራችን የሚመሰክረው ምን ይሆን? ቃሉ እንደሚለን ነን? እኛ ስለራሳችን እንደምንለው ነን? በሕይወታችን የሚታየው ፍሬ የሥጋ ወይስ የመንፈስ ፍሬ ነው? ይህንን ጉዳይ አበክረን ልናስብበት ይገባናል።

# ክፍል አስር

ኃጢአት - የደኅንነት አስፈላጊነት
ለአይሁድ (ሮሜ 3፥1-8)

እንግዲህ የአይሁዳዊ ብልጫው ምንድር ነው? ወይስ የመገረዝ ጥቅሙ ምንድር ነው? በሁሉ ነገር ብዙ ነው። አስቀድሞ የእግዚአብሔር ቃላት አደራ ተሰጡአቸው። ታዲያ ምንድር ነው? የማያምኑ ቢኖሩ አለማመናቸው የእግዚአብሔርን ታማኝነት ያስቀራልን? እንዲህ አይሁን፤ በቃልህ ትጸድቅ ዘንድ ወደ ፍርድ በገባህም ጊዜ ትረታ ዘንድ ተብሎ እንደ ተጻፈ፥ ሰው ሁሉ ውሸተኛ ከሆነ እግዚአብሔር እውነተኛ ይሁን። ነገር ግን ዓመፃችን የእግዚአብሔርን ጽድቅ የሚያስረዳ ከሆነ ምን እንላለን? ቍጣን የሚያመጣ እግዚአብሔር ዓመፀኛ ነውን? እንደ ሰው ልማድ እላለሁ። እንዲህ አይሁን፤ እንዲህ ቢሆን እግዚአብሔር በዓለም እንዴት ይፈርዳል? በእኔ ውሸት ግን የእግዚአብሔር እውነት ለክብሩ ከላቀ ስለምን በእኔ ደግሞ እንደ ኃጢአተኛ ገና ይፈርድብኛል? ስለ ምንስ መልካም እንዲመጣ ክፉ አናደርግም? እንዲሁ ይሰድቡናልና አንዳንዱም እንዲሁ እንድንል ይናገራሉና። የእነርሱም ፍርድ ቅን ነው።

በጥናት አንድ ላይ፥ አይሁድ ከአሕዛብ ባልተለየ ሁኔታ ውስጥ መገኘታቸውንና በተለይም ደግሞ ከደህንነት አኳያ፥ እነርሱም ልክ እንደ አሕዛብ የጠፉ መሆናቸውን ጳውሎስ መግለጹን ተመልክተናል።

ይህ አባባል ታድያ፥ “እስራኤላውያን በእግዚአብሔር ፊት የተለየ ስፍራ የላቸውም እንዴ?” የሚል፥ ወይም ጳውሎስ በሮሜ 3፥1 እንደ ጠቀሰው፥ “እንግዲህ የአይሁዳዊ ብልጫ ምንድን ነው ... ? የሚል ጥያቄ ሊያስነሳ ይችላል።

1. በዚህ ጉዳይ ላይ የእርስዎ መረዳት ምንድን ነው? እስቲ የተረዱትን ወይም የሚመስልዎትን ለቡድኖ አባላት ያካፍሉ።



2. ጳውሎስ በዚህ የሮሜ መልዕክት ክፍል ውስጥ እራሱ ላነሳው ጥያቄ ምላሽ ለመስጠት የሞከረ ይመስልዎታል? ምን ብሏል? (ሮሜ 3፥1)

በቁጥር ሁለት ላይ ጳውሎስ የአይሁዳዊ ብልጫ ምን እንደሆነ ሲገልጽ፥ “በሁሉ ነገር ብዙ ነው።” በማለት ነበር።

3. በሮሜ 3፥2 እንደ ተገለጸው፥ የአይሁድን ብልጫ ከሚያረጋግጡ “ብዙ” ነገሮች መካከል አንዱ ምንድን ነው?

አስቀድሞ የእግዚአብሔር ቃል አደራ ተሰጥቷቸዋል (ሮሜ 3፥2፤ መዝሙር 147፥19-20)። የእግዚአብሔር አሳብ ወደ አሕዛብ ከመምጣቱ አስቀድሞ ነበር ለአይሁድ የተሰጠው። ስለዚህ፥ አይሁድ ይህንን ከፍተኛ አደራ ያካተተ ትልቅ እድል በማግኘት ቀዳሚነት ወይም ብልጫ እንደነበራቸው ያሳያል። ምንም እንኳ፥ “ቃሉን” ሲል ብሉይ ኪዳንን ቢሆንም፥ ጌታችን ኢየሱስ በታላቁ ትእዛዝ ላይ እንደገለጸው ወንጌል እንኳ አስቀድሞ የተሰበከው ለአይሁድ ነበር።

ጳውሎስ የአይሁድ ብልጫ በሁሉ ነገር ብዙ እንደሆነ ቢጠቅስም እንኳ የብልጫውን ዝርዝር በስፋት አላቀረበም። ሆኖም ግን ምናልባት ከዚህ ዝርዝር ውስጥ ልናካትተው ከምንችለው ጉዳይ መካል አንዱ በእግዚአብሔር ፊት ተቀባይነት የማግኘት ብልጫ አንዱ ሊሆን ይችላል።

“ያዕቆብን ወደድሁ ኤሳውን ግን ጠላሁ ... ።” ተብሎ እንደ ተጻፈ፥ እግዚአብሔር አይሁድን ከሌላው ሕዝብ ለይቶ መርጦ ነበር። ስለዚህ፥ አይሁድ የእግዚአብሔር ሕዝብ በመባል የተለየ ሥፍራ ነበራቸው። ስለዚህ፥ ማንም ግለሰብ ከዚህ ልዩ በኀነት ከእግዚአብሔር ከሚቀበለው ሕዝብ መካከል ለመቀላቀል፥ የቀድሞ ባህሉንና ዜግነቱን ቀይሮ የግድ አይሁዳዊ መሆን ነበረበት። ወንድ ከሆነ ደግሞ የሥጋ ግርዛት ማድረግም ነበረበት።

በትውልድ አይሁዳዊ የነበሩት ግን ዝም ብሎ በመወለድ ይህን ብልጫ ያገኛሉ። ችግሩ ግን ይህን ብልጫ ወይም ልዩ እድል ሊጠቀሙበት አለመቻላቸው ነበር።

4. ሮሜ 2፥3 ላይ በተገለጸው መሠረት የአይሁድ ዋና ችግር ምን ነበር?

የአይሁድ ችግር፥ <u>አለመታመን (ታማኝ ሆኖ አለመገኘት)</u> መሆኑን ጳውሎስ በቁጥር ሶስት ላይ በመከራከሪያ ጥያቄ መልክ ባቀረበው አሳብ ላይ ይገልጻል።

ምንም እንኳ አይሁድ የበረከት ጥቅል የሆነውን የእግዚአብሔርን ቃል ቢቀበሉም፥ አለመታመናቸው ግን የቃሉን በረከት ወይም ከሌላው ሕዝብ በተለየ የተሰጣቸውን ብልጫ እንደሚገባ ሊጠቀሙበት አልቻሉም። ምክንያቱም፥ "የእግዚአብሔርን ቃል በተቀበሉበት መንፈስ አልተገኙም።" ወይም በሌላ አባባል፥ ለተሰጣቸው ልዩ መብትና አደራ ብቁ ለመሆን አልታመኑም ነበር።

ወገኖች ቃሉን መቀበላችን በመታዘዛችን ካልተተረጎመ ቃሉ ለሕይወታችን ምንም ፋይዳ የማይሰጥ ሊሆን ይችላል። ስለዚህ፥ ቃሉን ማጥናት፣ ማሰላሰልና በተግባር ማዋል የግድ ያስፈልጋል።

"አንድ ከጥሩ ቤተሰብ የመጣ ወጣት የታወቀ ኮሌጅ ውስጥ ወላጆቹ እየከፈሉለት እንዲማር መደረጉና በሌሎች ትምሕርት ቤቶች ውስጥ ሊገኙ በማይችሉ ጠቃሚ 'ሪሶውርሶች' እየተደገፈ ሁነኛ በሆኑ አስተማሪዎች መማሩ ብቻ ውጤታማ ሊያደርገው አይችልም። ምክንያቱም ለውጤታማነቱ የቀረበለትን እድል በመመንዘር እንደሚገባ መጠቀም ይኖርበታል።"

ክርስትናችንም እንደዚሁ ነው። በለመለመ መስክ የሚያሳድረን፣ በእረፍት ውሃ ዘንድ የሚመራን፣ በጽድቅ መንገድ የሚመራን ጌታ ቢኖረንም አብረነው ካልተራመድን፣ በመንገዱም ካልተከተልነው ብልጫችን ከንቱ ነው የሚሆነው። ቃሉን በጣም ብናደንቅና እንደ ጉድ ብንናገረው አድራጊዎች ካልሆንን የቃሉ በረከት ሊያልፈን ይችላል። ስለዚህ፥ ሁልጊዜ እንደቃሉ ልንሆን የግድ ነው።

በቁጥር ሦስት ላይ ጳውሎስ፥ " ... አለማመናቸው የእግዚአብሔርን ታማኝነት ያስቀራልን? በማለት ላነሳው ጥያቄ የሚሰጠው ምላሽ፥ "እንዲህ አይሁን።" ወይም በሌላ አባባል፥ "በፍጹም አያስቀርም።" የሚል ነው። ጳውሎስ በዚህ ክፍል በገለጸው መሠረት እንዲያውም የእግዚአብሔርን ታማኝነት የበለጠ የሚያጸናው እንደሆነ ነው የሚጠቁመው።

5. ሰዎች ታማኝ ባልሆኑበት ሁኔታ ውስጥ የእግዚአብሔር ታማኝነት የሚጸናው እንዴት ይመስልዎታል? በጳውሎስ ገለጻ መሠረት እግዚአብሔር ታማኝነቱን በሁለት መንገድ ያጸናዋል። ጳውሎስ የጠቀሳቸውን፥ የእግዚአብሔር ታማኝነት የሚጸናባቸውን እነዚህን ሁለት መንገዶች ይጠቁሙ።



- ለኃጢአተኛ የኃጢአቱን ዋጋ በመስጠት
- ለሚወዱት ደግሞ በረከትን በመስጠት

የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን በዘመናት መካከል እንደጸና የሚኖር ነው። እግዚአብሔር አይለዋወጥም፤ ሁልጊዜ እንደቃሉ ይኖራል። ስለዚህ፥ በቃልኪዳኑ ክልል ወይም በፊቱ ለሚመላለስ በረከት ሲያገኝ፣ ከቃል ኪዳኑ ክልል የወጣ ግን የቃልኪዳኑ ተጠቃሚ ካለመሆን አልፎ በውጭ የሚገኝ መቅሰፍት ሊያገኘው ይችላል። (በግብጽ የሞት መልአክ በመጣ ጊዜ፥ እስራኤላውያን የደሙ ምልክት ካለበት ከቤታቸው ውጪ ቢገኙ፥ ለግብጽ የመጣው መቅሰፍት እነርሱንም ሊያገኛቸው እንደሚችለው ማለት ነው።)

6. በቁጥር አራት ላይ፥ "ሰው ውሸተኛ ከሆነ እግዚአብሔር እውነተኛ ይሁን።" ይላል። ጳውሎስ ይህን ሲል ምን ለማለት ፈልጎ ነው?

በሮሜ 3፥4 ላይ ጳውሎስ፥ "እግዚአብሔር እውነተኛ" ሲል የእግዚአብሔር ቀጥተኝነት ትክክለኛ መሆኑን ለመግለጽ ነው። በዚህ ክፍል "እውነተኛ" የሚለው ፥ እውነት የሆነውን የእግዚአብሔርን ማንነት ለመግለጽ ነው። እግዚአብሔር እውነት ስለሆነ ከእርሱ የሚወጣ ሁሉ እውነት ነው። ይህን የእግዚአብሔርን ባህሪ ደግሞ ምንም ነገር አይቀይረውም። ስለዚህ፥ የእርሱን ታማኝነት ሊያስቀር የሚችል ምንም ነገር የለም!

በመዝሙር 51፥3-4 ዳዊት፥ "እኔ መተላለፌን አውቃለሁና፥ ኃጢአቴም ሁልጊዜ በፊቴ ነውና። አንተን ብቻ በደልሁ፥ በፊትህም ክፉትን አደረግሁ፥ በነገርህም ትጸድቅ ዘንድ በፍርድህም ንጹሕ ትሆን ዘንድ።" በማለት በእርሱ አለመታመን የእግዚአብሔርን ታማኝነት፣ በእርሱ ስሕተተኛነት የእግዚአብሔርን ትክክለኛነት ወይም የማይለወጥ እውነተኛነት በግልጽ ሲናገር እናያለን።

በተመሳሳይ የአይሁዳዊ አለመታመን የእግዚአብሔርን በቃል ኪዳኑ ታማኝ መሆን አልለወጠውም። ይልቁን በጥፋታቸው ተጸጽተው በተመለሱ ቁጥር በምሕረቱ ይቀበላቸው ነበር። በተጨማሪም፥ እግዚአብሔር ገና በገነት የሰጠውን ቃልኪዳን፥ ልጁን ኢየሱስን በመስጠት ፈጽሞታል። ይህ የእግዚአብሔርን የማይለወጥ ታማኝነት ወይም እውነተኛነት ይገልጻል። እርሱ ቃል ኪዳኑን በምንም ሁኔታ ውስጥ አይለውጥም።

ስለዚህ፥ ዳዊት እንደሚናገር ወደ እግዚአብሔር ቃል ኪዳን ለሚመለስ ሁሉ የእግዚአብሔር ታማኝነት በይበልጥ ጸንቶ ይታያል። ዛሬም ደግሞ እንዲሁ ነው፤ የእግዚአብሔር ታማኝነት ዛሬም ብዙ ነው (ዮሐንስ 1፥9-12)

7. በሮሜ 3፥5-8፥ ጳውሎስ፥ አይሁድ ሊያነሱት የሚችሉትን ሌላ የመከራከሪያ ነጥብ በጥያቄ መልክ በማንሳት ትክክለኛውን ምላሽ ይሰጣቸዋል። በዚህ ክፍል ጳውሎስ በጥያቄ መልክ ያነሳው የአይሁድ መከራከሪያ ሐሳብ ምን ሊሆን ይችላል? በዚህ ዘመን ይህ ጥያቄ ምን አይነት ተግባራዊ ገጽታ ይዞ ሊነሳ ይችላል? ለዚህ ጥያቄ ጳውሎስ የሚሰጠው ምላሽ ምንድን ነው?

____________________________________________________________

____________________________________________________________

____________________________________________________________

____________________________________________________________

በጳውሎስ አገላለጽ መሠረት አይሁድ ሊያነሱት የሚችሉት ጥያቄ፥ “ኃጢአታችን የእግዚአብሔርን ጽድቅ የሚገልጽ ከሆነ እንዴት ይፈረድብናል?” የሚል ሊሆን ይችላል። በሌላ አገላለጽ ደግሞ፥ “እግዚአብሔር በሰዎች ኃጢአትና ውድቀት የሚከብር ከሆነ ሰዎች በሚሰሩት ኃጢአት ምንም ተጠያቂነት የለባቸውም ማለት ነው? እግዚአብሔር እንዲከብር ሰዎች ኃጢአት ማድረግ አለባቸው ማለት ነው?”የሚል ሊሆን ይችላል።

በዚህ ዘመን ስለሰው ሙብት የቆሙ በሚመስላቸው ሰዎች፥ “ውሸተኛ በውሸቱ መጠየቅ የለበትም፣ ግብረ ሰዶማዊው በግብረ ሰዶማዊነቱ መኮነን አይገባውም፣ ነፍሰ ገዳይና ክፉ የሚሰሩ ሁሉ እግዚአብሔር ታማኝነቱን ሊገልጽባቸው ስለሆነ ልንረዳቸው ይገባል።” በማለት፥ ሊከራከሩ ወገባቸውን ታጥቀው የሚነሱበት ጊዜ አለ።

የጳውሎስ፥ በዚህ ጉዳይ ሊነሱ የሚችሉ ጥያቄዎችን ግልጽና እርግጠኛ በመሆን መንገድ ለመዝጋት፥ “ እንዲህ አይሁን!” በሚል መልሶታል። በዚህ ምላሹ ላይ፥ መልካም ነገር ለማግኘት ክፉ መሥራት እንደሌለብንና አውቀን ክፋትን የምንሰራ ከሆነ እግዚአብሔር በጽድቁ እንደሚፈርድብን ይገልጻል።

8. ከዛሬው ጥናት ምን ተገነዘቡ?

____________________________________________________________

____________________________________________________________

____________________________________________________________

____________________________________________________________

____________________________________________________________



# ክፍል አሥራ አንድ

## ኃጢአት - የደኅንነት አስፈላጊነት ለዓለም ሁሉ(3፥9-20)

እንግዲህ ምን ይሁን? ከእነርሱ እንበልጣለንን? ከቶ አይደለም፤ አይሁድም የግሪክ ሰዎችም ሁሉ ከኃጢአት በታች እንደ ሆኑ አስቀድመን ከሰናቸዋልና፤ እንዲህ ተብሎ እንደ ተጻፈ። ጻድቅ የለም አንድ ስንኳ፤ አስተዋይም የለም፤ እግዚአብሔርንም የሚፈልግ የለም፤ ሁሉ ተሳስተዋል፥ በአንድነትም የማይጠቅሙ ሆነዋል፤ ቸርነት የሚያደርግ የለም፥ አንድ ስንኳ የለም።

ጉሮሮአቸው እንደ ተከፈተ መቃብር ነው፥ በምላሳቸውም ሸንግለዋል፤ የእባብ መርዝ ከከንፈሮቻቸው በታች አለ፤ አፋቸውም እርግማንና መራርነት ሞልቶበታል፤ እግሮቻቸው ደምን ለማፍሰስ ፈጣኖች ናቸው፤ ጥፋትና ጉስቁልና በመንገዳቸው ይገኛል፥ የሰላምንም መንገድ አያውቁም። በዓይኖቻቸው ፊት እግዚአብሔርን መፍራት የለም።

አፍም ሁሉ ይዘጋ ዘንድ ዓለምም ሁሉ ከእግዚአብሔር ፍርድ በታች ይሆን ዘንድ ሕግ የሚናገረው ሁሉ ከሕግ በታች ላሉት እንዲናገር እናውቃለን፤ይህም የሕግን ሥራ በመሥራት ሥጋ የለበሰ ሁሉ በእርሱ ፊት ስለማይጸድቅ ነው፤ ኃጢአት በሕግ ይታወቃልና።

በተለይ በሰለጠነው አለም በሚገኙና በክርስቶስ በማያምኑ ኅብረተሰቦች ዘንድ፥ እግዚአብሔር እንደሌለ፣ ካለ ደግም በሰዎች መከራና ስቃይ ግድ እንደማይሰጠው፥ ወይም ጨካኝ እንደሆነ ተደርጎ ይገመታል። ስለዚህ፥ ስለጌታ ሊመሰከርላቸው ሲሞከር፥ “በአለም ያለውን ቀውስ፣ የሰዎችን መከራና ጉዳት እየተመለከቱ፥ የፍቅር አምላክ እግዚአብሔር አለ ማለት እንዴት ይቻላል?” ይላሉ።

ጳውሎስ እንዲህ አይነቱን ክስ ለመከላከል፥ አሕዛብ ለክፋት የተተዉት በራሳቸው ምርጫ እንደሆነ፣ አይሁድም ከክብር የጎደሉት በራሳቸው አለመታመን እንደሆነ በማሳወቅ የእግዚአብሔርን ጻድቅነት ገልጿል።

በጥናት አንድና ሁለት ላይ፥ ሐዋርያው ጳውሎስ የአሕዛብንና የአይሁድን ሁኔታ በተናጠል መግለጹን ተገንዝበናል። በሮሜ 3፥9-20 ደግሞ ሁሉንም ኅብረተሰብ በአንድ በመጠቅለል፥ የሰው ዘር ሁሉ ከኃጢአት የተነሳ በጥፋት ጎዳና ላይ እንዳለ ገልጿል።

1. በቁጥር ዘጠኝ ላይ ጳውሎስ፥ “እንግዲህ ምን ይሁን?” የሚለው ምኑን ነው?

በቁጥር ዘጠኝ ላይ፥ “... አስቀድመን ከሰናቸዋል።” በማለት ሁሉም የሰው ዘር ሊከሰስ የሚችልበትን ምክንያት ይዘረዝራል።

2. እነዚህን የክስ ምክንያቶች ይዘርዝሯቸው (11-18)።

የክሱ ምክንያቶች:-

- የሰው ዘር የማያስተውልና ጌታን የማይፈልግ መሆኑ (ቁ. 11)
- የሰው ዘር መልካም የማይገኝበት መሆኑ (ቁ. 12)
- የሰው ዘር ክፉ አንደበት ወይም ምላስ ያለው መሆኑ (ቁ. 13)
- የሰው ዘር አንደበት እርግማንና የምሬት ንግግር የሞላው መሆኑ (ቁ. 14)
- የሰው ዘር የሰውን ነፍስ ለማጥፋት የፈጠነ መሆኑ (ቁ. 15)
- የሰው ዘር ጥፋትና ጉስቁልናን የሚፈልግ መሆኑ (ቁ. 16)
- የሰው ዘር የሰላምን መንገድ የማያውቅ መሆኑ (ቁ. 17)
- የሰው ዘር እግዚአብሔርን የማይፈራ መሆኑ (ቁ. 18)

በቁጥር 11 ላይ ሰው ሁሉ የማያስተውልና ጌታን የማይፈልግ እንደሆነ ተገልጿል። ይህ ጉድለት ሰዎች ሁሉ የታወሩ ወይም በጨለማ የሚኖሩ መሆናቸውን ያስገነዝባል። ስለዚህ፥ ሰዎች ሁሉ በጨለማ እየተደናበሩ የሚኖሩ እውሮች ናቸው፤ አንዱ ለሌላው መሪ ሊሆን ቀርቶ ራሱን ለመምራት አይችልም ነበር፤ ሁሉም የታወረ ልብ ስላላቸው እግዚአብሔርን መፈለግ ተስኗቸዋል።



3. እንግዲህ ሰው ሁሉ እግዚአብሔርን ማየትና መፈለግ ካልቻለ፥ መፍትሄው ምን ሊሆን ይችላል?(ሉቃስ 19፥10)

ኃጢአተኛ ሰው እግዚአብሔርን መፈለግ ካልቻለ ያለው ብቸኛ አማራጭ እግዚአብሔር ራሱ ሰውን ፈልጎ መምጣት ነበር።

ሰው ሁሉ የማያስተውልና እግዚአብሔርን የማይፈልግ ከሆነ እንግዲህ፥ ማንም በራሱ ጥረትና ፍለጋ እግዚአብሔርን ሊያገኘው አይችልም ማለት ነው።

የአዳም ዘር ባቢሎን ተብሎ በተጠራው ሥፍራ ላይ፥ ሰማይ የሚደርስ ግንብ ለመገንባት እንደሞከሩ፥ ዛሬም ማንም ሰው ምንም አይነት ከፍተኛ የአምልኮ ግንቦች ቢገነባም እግዚአብሔር ጋ ፈጽሞ ሊደርስ አይችልም።

4. በቁጥር 12፥ የሰው ዘር ምንም መልካም የማይገኝበት መሆኑ ተገልጿል። እስቲ የዚህን አገላለጽ ተግባራዊ ትንታኔ ለቡድንዎ አባላት ያካፍሉ።

በሰው አይን ሲታይ መልካም የሚባሉ ተግባሮችን የሚፈጽሙ ነገር ግን ያልዳኑ ግለሰቦች ሊኖሩ ይችላሉ። ነገር ግን እግዚአብሔር በሰው ሚዛን ስለማይመዝን እኛ በመልካምነታቸው የመሰከርንላቸውን እርሱ ግን ሊያቃልላቸው ይችላል።

በመጨረሻው ዘመን በጌታ ፊት ቀርበው የሰሩትን መልካም ሥራ ቢዘረዝሩም እንኳ፥ “አላውቃችሁም!” የሚባሉ ሰዎች እንዳሉ ማቴዎስ በጻፈው ወንጌል ላይ ተገልጿል። ይህ ሐሳብ ምናልባት አንድን ነገር መልካም የሚያሰኘው ተግባሩ ብቻ ሳይሆን የተግባሩም ምክንያት እንደሆነ ሊገልጽ ይችላል።

“ሰው ፊትን ያያል፥ እግዚአብሔር ግን ልብን ይመረምራል ... ” እንደሚል ራስ ወዳድ የሆነው ሰው ለግል ርካታ የሚያከናውናቸው ነገሮች ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት ተፈትሸው የሚቀሉ ይሆናል። ለሰው ብሎ የሚያስመስልም ሽፋኑ ይገለጥና ውስጡ ባዶ ሆኖ ይታያል ...

በቁጠር 13፥ ሰው ክፉ ምላስ ወይም አንደበት ያለው መሆኑን ሲገልጽ፥ “ጉሮሮአቸው እንደ ተከፈተ መቃብር ነው፥ በምላሳቸውም ሸንግለዋል፤ የእባብ መርዝ ከከንፈሮቻቸው በታች አለ።” ይላል።

ይህ አባባል፥ ኃጢአተኛ ሰው ሙት ስለሆነ ከአንደበቱ የሚወጣው ልክ ከመቃብር እንደወጣ የሞተና የከረፋ ነገር መሆኑን የሚገልጽ ነው።

በተጨማሪም ደግሞ ልክ እባብ ሁኔታ ሲያስገድደው፥ በምላሱ ሥር ካለው ከረጢት ውስጥ መርዙን እንደሚረጭ፥ ኃጢአተኛ ሰውም እንዲሁ ሁኔታዎች ሲነካኩት የሚተፋው መርዝ በምላሱ ላይ አለው። ይህ መርዝ ሰዎችን እየነደፈ ጉዳት ያስከትልባቸዋል። (ምሳሌ5፥3-4)

5. በቁጥር 15 ደግሞ ሰው ርግማንና የምሬት ንግግር የሞላው እንደሆነ ይገልጻል። ርግማንና የምሬት ንግግር ክፉ የሆነበትን ምክንያት ያስረዱ?

ርግማንና የምሬት ንግግር እንኳ በእግዚአብሔር ጆሮ ይቅርና በሰው ጆሮም በጣም የሚቀፍ ንግግር ነው። አንድ ሰው በተደጋጋሚ ሲራገምና የምሬት ንግግር ከአንደበቱ ሲያወጣ መስማት በጣም የሚያስቀይም ነው።

በቁጥር 15፥ ሰዎች የሌላን ሰው ነፍስ ለማጥፋት የፈጠኑ መሆናቸውን ይገልጻል። ይህ አባባል በአለማችን የታሪክ መዝገብ ቦታ ያጣበቡትን የርስ በርስ ጦርነቶች፣ በሃገራት መካከል የተካሄዱትንና አለም አቀፍ ይዘት ያላቸውን ጦርነቶች የሚያስታውሰን ነው። ኃጢአተኛ ሰው እግዚአብሔርን ስለማይፈራ (መዝሙር 36፥1)፥ ጠላቴ ነው የሚለውንና የሚጠላውን ሰው ለማጥፋት በቀላሉ ሊነሳ ይችላል።

6. በቁጥር 16 ደግሞ ሰው ጥፋትንና ጉስቁልናን የሚፈልግ መሆኑ ተጠቅሷል። ይህን እውነታ ሊያንጸባርቁ ከሚችሉ ሁኔታዎች መካከል አንዱን ለመግጽ ይሞክሩ።

የዜና አውታሮች ጥፋትን፣ ቀውስንና ጉስቁልናን ለማተት የሚያደርጉት ወከባ የኃጢአተኛ ሰውን የጥፋት ፍላጎት ከሚያሳዩን መካከል አንዱ ነው።



በቁጥር 16 ጳውሎስ፥ የሰው ዘር የሰላምን መንገድ የማያውቅ መሆኑን ይገልጻል። ይህ ደግሞ በአለማችን ሰላምን የማስፈን ሚና የተሰጠው የተባበሩት መንግስታት ጥረት እስካሁን የሚፈለገውን ሰላም ያለማምጣቱን ምክንያት ያሳየናል።

7. በቁጥር 18 ደግሞ፥ ኃጢአተኛ ሰው እግዚአብሔርን የማይፈራ መሆኑ ተጠቅሷል። እንዲህ አይነት ሰው ምን አይነት ገቢራዊ ሕይወት የሚኖረው ይመስልዎታል?

8. ጳውሎስ በቁጥር 3፥1-18 የዘረዘራቸውን ማስረጃዎች ተመርኩዞ በቁጥር 19ና 20 ላይ ሊገልጽ ወይም ሊያስገነዝብ የፈለገውን መሠረታዊ ሐሳብ ለማብራራት ይሞክሩ?

በዚህ ክፍል ውስጥ ጳውሎስ አሕዛብ ሆኑ አይሁድ ከተጠያቂነት ሊያመልጡ በማይችሉበት ሁኔታ ውስጥ እንዳሉ በመግለጽ ሰው ሁሉ ኃጢአተኛ ወይም እግዚአብሔርን የበደለ መሆኑን ያስገነዝባል።

አሕዛብ የጥፋትን መንገድ በመምረጣቸው፥ አይሁድም ደግሞ ሕግን በመተላለፋቸው ምክንያት አንዳቸውም የመከላከያ ቃል መተንፈስ አይችሉም፤ የሚያመካኙትና የሚመልሱት ምንም የላቸውም። ሁሉ በደለኛ ስለሆነ ጻድቅ ነኝ ብሎበእግዚአብሔር ፊት የሚቆም ወይም የሚመካ ፈጽሞ አልተገኘም... አይገኝምም!።

9. ከዛሬው ጥናት ምን ተገነዘቡ?

# ክፍል አሥራ ሁለት

ጽድቅ በእምነት - የደኅንነት መሰፈርት
በእምነት የሚሆን የእግዚአብሔር ጽድቅ (3፥21-31)

አሁን ግን በሕግና በነቢያት የተመሰከረለት የእግዚአብሔር ጽድቅ ያለ ሕግ ተገልጦአል፥ እርሱም፥ ለሚያምኑ ሁሉ የሆነ፥ በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን የሚገኘው የእግዚአብሔር ጽድቅ ነው፤ ልዩነት የለምና፤ ሁሉ ኃጢአትን ሠርተዋልና የእግዚአብሔርም ክብር ጎድሎአቸዋል፤ በኢየሱስ ክርስቶስም በሆነው ቤዛነት በኩል እንዲያው በጸጋው ይጸድቃሉ። እርሱንም እግዚአብሔር በእምነት የሚገኝ በደሙም የሆነ ማስተስሪያ አድርጎ አቆመው፤ ይህም በፊት የተደረገውን ኃጢአት በእግዚአብሔር ችሎታ ስለ መተው ጽድቁን ያሳይ ዘንድ ነው፥ ራሱም ጻድቅ እንዲሆን በኢየሱስም የሚያምነውን እንዲያጸድቅ አሁን በዚህ ዘመን ጽድቁን ያሳይ ዘንድ ነው። ትምክህት እንግዲህ ወዴት ነው? እርሱ ቀርቶአል። በየትኛው ሕግ ነው? በሥራ ሕግ ነውን? አይደለም፥ በእምነት ሕግ ነው እንጂ። ሰው ያለ ሕግ ሥራ በእምነት እንዲጸድቅ እንቆጥራለንና። ወይስ እግዚአብሔር የአይሁድ ብቻ አምላክ ነውን? የአሕዛብስ ደግሞ አምላክ አይደለምን? አዎን፥ የተገረዘን ስለ እምነት ያልተገረዘንም በእምነት የሚያጸድቅ አምላክ አንድ ስለ ሆነ የአሕዛብ ደግሞ አምላክ ነው። እንግዲህ ሕግን በእምነት እንሽራለንን? አይደለም፤ ሕግን እናጸናለን እንጂ።

በክፍል አሥራ አንድ ላይ እንዳየነው፥ ጳውሎስ በዝርዝር ባቀረበው ማስረጃ፥ ሰዎች ሁሉ ኃጢአተኛ መሆናቸውንና፥ ለጽድቅ ተስፋ የሚያደርጉት መልካም ሥራ ሊኖራቸው እንደማይችል እንዲሁም ሕግን ለመጠበቅ መጣጣር ሊያጸድቃቸው እንደማይችል አረጋግጧል።

ነገር ግን ከቁጥር ሃያ አንድ በኋላ በሚያነሳው ነጥብ፥ ሰው በራሱ ሥራና በሕግ ሳይሆን እግዚአብሔር ባዘጋጀው የጽድቅ መንገድ ብቻ ሊጸድቅ የሚችል መሆኑን አስታውቋል።

1. በሮሜ 3፥ 21 ጳውሎስ፥ "አሁን ግን ..." ምን ሆነ ነው የሚለው? ይህን አሳብ በራስዎ አባባል ይግለጹት።

________________________________________

________________________________________



"አሁን ግን ... " የሚለው ቃል፥ ጳውሎስ አስቀድሞ ባቀረበው ዝርዝር ማስረጃ ያረጋገጠው አሳዛኝ ጉዳይ ላስጨነቀውና ግራ ሊጋባው ሰው የተስፋን ጮራ የሚያሳይ ቃል ነው።

ምን እንኳ በበደሌ ምክንያት የወደቅሁና ተስፋ የሌለኝ የነበርኩ ቢሆንም፣ ብልቶቼን በእግዚአብሔር ሕግ ገርቼ በመኖር ለመጽደቅ የማደርገው ጥረት ስለማይሳካልኝ ተጨንቄ የነበርኩ ቢሆንም፥ ቆጥሬ ለመዝለቅ እስከማልችል ድረስ ሕግ የጥፋቴን ዝርዝር በፊቴ እያቀረበ የሚያውከኝ ቢሆንም፥ "አሁን ግን ..." የተስፋዬ ጮራ ተከፍቷል። የእግዚአብሔር ጽድቅ <u>ያለ ሕግ</u> ተገልጧል።

2. ጳውሎስ <u>ያለ ሕግ</u> ሲል ምን ለማለት የፈለገ ይመስልዎታል? (እግዚአብሔር ሕጉን ሻረ ወይም አረገበ ማለት ነው?)

________________________________________

________________________________________

________________________________________

________________________________________

ጳውሎስ ያለ ሕግ ሲል፥ የእግዚአብሔር ጽድቅ በክርስቶስ የጽድቅ ሥራ ሙሉ ለሙሉ ተጠናቆ የተገለጠ (ማቴዎስ 5፥17) መሆኑንና፥ ሰው ምንም ሳያዋጣበት ወይም ጭማሪ ሳያደርግበት እንዲሁ በነጻ የሚቀበለው መሆኑን ለማስገንዘብ ነው።

በክርስቶስ የጽድቅ ሥራ ሙሉ ለሙሉ ተጠናቆ የተገለጠው የእግዚአብሔር ጽድቅ፥ ግብታዊ (ድንገተኛ ክስተት) ሳይሆን፥ አስቀድሞ በሕግና በነቢያት የተነገረ ነው። በሌላ አባባል፥ ሕግና ነቢያት አስቀድመው ይጠቁሙ የነበረው፥ አሁን በክርስቶስ የጽድቅ ሥራ ተጠናቆ ወደ ቀረበው ጽድቅ ነው። ስለዚህ፥ በራሳችን አቅም ልንጠብቀው የምንሞክረው ሕግ ጽድቅን አያስገኝልንም። ጽድቃችን በድካም ቢዘጋጅም (ማቴዎስ 16፥21፤ 2ኛ ቆሮንቶስ 13፥4) በክርስቶስ በኩል ያለ ድካም ልንቀበለው ነቢያት ከሩቁ ጠቁመዋል።

3. ሕግና ነቢያት ስለ ክርስቶስ ከመሰከሯቸው መካከል እርስዎ የሚያስታውሷቸውን ጥቂት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ይጥቀሱ

________________________________________

________________________________________

________________________________________

________________________________________

ዘፍጥረት 3፥15፤ ኢሳይያስ 7፥14፤ 53፥3፤ መዝሙር 16፥10-11፤ ኢሳይያስ 9፥7
እግዚአብሔር በአዲስ ኪዳን በክርስቶስ የጽድቅ ሥራ የገለጠው የተሟላ ጽድቅ፥ በሕግ ውስጥ ተነግሮ ነበር። አይሁድ ግን ይህንንን ዕውነት እንዲያዩበት የተሰጣቸውን ሕግ ተመክተው ከእግዚአብሔር ተስፋ ወይም አሳብ ጨርሰው ራቁ።

ስለዚህ፥ ሐዋርያው ጳውሎስ ይህ የተመኩበት ሕግ የሚመሰክረው፥ በክርስቶስ ስለተገለጠው የተሟላ ጽድቅ መሆኑን በማስገንዘብ ማብራሪያውን አቅርቧል።

4. ጳውሎስ በሮሜ 3፥22 እንደሚያስገነዝበው፥ በክርስቶስ የተገለጠው ጽድቅ ለሰዎች የሚለቀቀው እንዴት ነው? ወይም በሰዎች ሕይወት የሚሰራው መቼ ነው?

## ባመንን ጊዜ የሚሆን ነው። (ቁ.22)

በሮሜ 3፥22 ላይ፥ ጽድቅ በክርስቶስ ኢየሱስ በማመን ሊሆን የሚችል ሳይሆን የሆነ መሆኑን ጳውሎስ ያረጋግጣል። በክርስቶስ በማመን ስለሆነ ደግሞ እንዲሆን የሚጨመር ነገር እንደሌለም ያመለክታል።

ለምሳሌ በአንድ ቤት ውስጥ የሚገኝ አምፖል (መብራት) ቀድሞውኑ በርቶ ካለ እኔ ስገባ እንደገና ላበራው መሞከር አይገባኝም፥ ምክንያቱም መብራቱ በርቷል!

በተመሳሳይ ክርስቶስ ሙሉ ለሙሉ ፈጽሞ ወይም አጠናቆ ያቀረበውን ጽድቅ እኛ ተቀብለን መጠቀም እንጂ፥ እንደገና በራሳችን ልናዘጋጀው ወይም የተሻለ አርገን ልናቀርበው አይገባንም። ጳውሎስ ይህ ጽድቅ፥ "የሚገኝ" መሆኑ ያሳሰበውም  እኛ የምናመጣው ሳይሆን ተዘጋጅቶ የተገለጠ ሆኖ ሳለ አለመታወቁ ነው።

5. በሮሜ 3፥22-23 ጳውሎስ ሰዎች ለራሳቸው ጽድቅ ማዘጋጀት ወይም በራሳቸው መጽደቅ የማይችሉበትን ምክንያትይገልጻል። ምክንያቱ ምንድን ነው?

## ምክንያቱ፥ ሁሉም ሰው ኃጢአተኛና የእግዚአብሔር ክብር የጎደለው መሆኑ ነው። ሰው ሁሉ በኃጢአት ስለተለወሰ የሚፈጽመው ተግባር ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት ጻድቅ ሆኖ እንዲታይ ሊያደርገው አይችልም።

ስለዚህ፥ መጀመሪያ የቆሸሸው ልብስ መውለቅና አዲስ ልብስ መለበስ አለበት፥ ይህ ልብስ ደግሞ ራሱ እግዚአብሔር ካላዘጋጀው በስተቀር በሰው አቅም ሊገኝ የሚችል አይደለም።



እጅግ ጥልቅ በሆነ ጉድጓድ ውስጥ የወደቀ ሰው በራሱ አቅም ለመውጣት አይችልም። ምክንያቱም፥ ጉድጓዱ እጅግ የራቀ ከመሆኑ የተነሳ ጉድጓድ ውስጥ የተቀመጠው ሰው፥ የፈለገውን ያህል ቢቧጥጥ፥ በራሱ ላይ ድካም ከመጨመር በስተቀር ራሱን ማውጣት አይችልም። ስለዚህ ከጉድጓዱ ውጪ የሆነ፣ ከወደቀበት ጥልቅ ጉድጓድ ለማውጣት ብቃትና ፈቃደኝነት ያለው ሌላ ታዳጊ ያስፈልገዋል ማለት ነው።

በተመሳሳይ፥ ጳውሎስ እንደሚናገረው፥ ሰው ሁሉ በፊተኛው አዳምና በራሱ ኃጢአት ውስጥ ስለተዘፈቀ በራሱ ጽድቅ ከኃጢአት ፍርድ ወጥቶ ከእግዚአብሔር ጋር ሊገናኝ አይችልም።

6. በሮሜ 3፥23፥ የእግዚአብሔርም ክብር ጎድሏቸዋል ሲል ምን ለማለት ይመስልዎታል?

## የእግዚአብሔር ባሕርይ ተካፋይ ከመሆንና ከእግዚአብሔር ጋር ካለው መልካም የኅብረት ትስስር ውስጥ ወጥተዋል ለማለት ነው።

የእግዚአብሔር ጽድቅ ማንም ስለተገባው፣ ስለለፋበት ወይም ስለተጋለት የሚያገኘው ሳይሆን፥ በቁጥር 24 ላይ ጳውሎስ እንደ ጠቀሰው፥ በኢየሱስ ክርስቶስ በሆነው ቤዛነት እንዲያው በጸጋው የተሰጠ ነው። ይህንን አባባል ባጭሩ ስንገልጸው ደግሞ፥ የእግዚአብሔር ጽድቅ እንዲሁ በነጻ የተሰጠን ነው እንላለን።

7. ታዲያ ምንም እንኳ የእግዚአብሔር ጽድቅ እንዲሁ በነጻ የተሰጠን ቢሆንም በነጻ የተዘጋጀ አይደለም። ይህንን በተመለከተ ጳውሎስ ምን ይናገራል (ቁ.25)

## ቤዛ የሚለው ቃል በግልጽ እንደሚያመለክተው የእግዚአብሔር ጽድቅ የተዘጋጀው እንዲሁ በነጻ ሳይሆን ዋጋ ተከፍሎበት ነው። ምክንያቱም ቤዛ ማለት ቀድሞ የራስ የነበረና ተወስዶ የነበረን ነገር ዋጋ ከፍሎ ማስመለስ ማለት ነው። በቁጥር 25 መሠረት ደግሞ ጌታ ኢየሱስ ቤዛ አድርጎ ያቀረበው ንጹህ ደሙን ነው።

እግዚአብሔር ፍትሐዊ በመሆኑ ኃጢአትን ሳይቀጣ አይተውም። መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚናገር ደግሞ የኃጢአት ደሞዝ (ቅጣቱ) ሞት ነው። ስለዚህ ልጁ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ደሙን በማፍሰስ ሞቶ ቅጣታችንን እንዲቀጣ በማድረግ እኛን ከፍርድ ነጻ አደረገን።

በሮሜ 3፥25-26፥ ከብዙ መታገስ በኋላ፥ በዚህ ዘመን ክርስቶስ ኢየሱስ ዋጋ እንዲከፍል ማድረጉ፥ የእግዚአብሔርን ጽድቅና ፍቅር የሚገልጥ መሆኑን ይጠቁማል። በቁጥር 27 ደግሞ በተለይ ከደኅንነት አኳያ ሰው በራሱ አቅም ተስፋ ቢስ መሆኑ የማያሻማ ዕውነት እንደሆነ በጥያቄ መልክ ተገልጧል።

8. በሮሜ 3፥21-30 በተገለጸው መሠረት ሰው በራሱ ለመጽደቅ የማይችለው ወይም ተስፋ ቢስ የሆነው ለምንድን ነው?

- ሰው ሁሉ ኃጢአተኛ ስለሆነ።
- ለሰው ሁሉ ኃጢአት ዋጋ መክፈል የቻለውና የከፈለው ጌታ ኢየሱስ ብቻ ስለሆነ ነው።

ቀደም ሲል እንዳነሳነው፥ ሰው ሕግን ሁሉ ያለ ምንም መጓደል ሊፈጽም ስለማይችል፥ ሰው በሕግ ሥራ እጸድቃለሁ ብሎ ሊመካ አይችልም። ኢየሱስ ክርስቶስ በከፈለው ዋጋ የተዘጋጀውን ጸድቅ አምኖ በመቀበል መጽደቅ ግን ይችላል። ይህ እድል ደግሞ ለሁሉ ሰው የተሰጠ እድል ነው።

9. በቁጥር 31 ጳውሎስ የሚያነሳው ጥያቄ ምንድን ነው? ለዚህ ጥያቄ የእርስዎ ምላሽ ምንድን ነው?

በእምነት መጽደቅ ሕግን የሚሽር አይደለም ምክንያቱም በማቴዎስ 5፥17 እንደ ተጠቀሰው ጌታ ኢየሱስ ሕግን ሊሽር ሳይሆን ሊፈጽም ነው የመጣው። ያደረገውም ይህንኑ ነው። እኛ ያቃተንን ሕግ እኛን በመወከል ሙሉ ለሙሉ ፈጽሞታል፤ የእግዚአብሔርንም ጽድቅ አርክቷል።

ስለዚህ እኛ በዚህ በክርስቶስ ጽድቅ በመሸፈን በእግዚአብሔር ፊት የመቅረብ ብቃትን አገኘን። ታዲያ አሁን ሕግ በእግዚአብሔር ፊት ተቀባይነትን ለማግኘት መለኪያ ባለመሆኑ፥ ክርስቶስ በኛ ውስጥ በመኖር ሕግ ሊያስገኝ ከሚችለው በላይ ከፍ እንድንል አስችሎናል። ምንም እንኳ ኃጢአት ሸንፈቱን በጸጋ ስላልተቀበለ አሁንም ደጃችንን ማንኳኳቱን ባይተውም በክርስቶስ ኃይል በአሸናፊነት መኖር ይቻለናል።



10. ከዛሬው ጥናት ምን ተገነዘቡ?

# ክፍል አሥራ ሦስት

ጽድቅ በእምነት - የደኅንነት መስፈርት
የአብርሃም ምሳሌነት (4፥1-5)

እንግዲህ በሥጋ አባታችን የሆነ አብርሃም ምን አገኘ እንላለን? አብርሃም በሥራ ጸድቆ ቢሆን የሚመካበት አለውና፥ ነገር ግን በእግዚአብሔር ዘንድ አይደለም። መጽሐፍስ ምን አለ? አብርሃምም እግዚአብሔርን አመነ ጽድቅም ሆኖ ተቈጠረለት። ለሚሠራ ደመወዝ እንደ ዕዳ ነው እንጂ እንደ ጸጋ አይቈጠርለትም፤ ነገር ግን ለማይሠራ፥ ኃጢአተኛውንም በሚያጸድቅ ለሚያምን ሰው እምነቱ ጽድቅ ሆኖ ይቈጠርለታል።

እምነት፣ ሥራና ሕግ፥ በጳውሎስ "ጽድቅ በእምነት" አስተምሕሮ ውስጥ ቁልፍ ስፍራ የያዙ ናቸው። እነዚህ ቃላት፥ እርስ በእርሳቸው ሊቃረኑ የሚችሉ ሁለት መሠረታዊ ሐሳቦችን ይገነባሉ። እነርሱም፦

- ሰው በሥራ (ሕግን በመጠበቅ) ይጸድቃል ወይም
- ሰው በእምነት ይጸድቃል

የሚሉት ናቸው።
አይሁድ፥ "ሕግን በሚገባ በመጠበቅ መጽደቅ ይቻላል።" ብለው ስለሚያምኑ፥ ሕግን ያጤኑና ይመረምሩ ነበር፣ የተለያዩ ሥርዓቶችንና ሕጎችን መስርተውም ነበር፣ ሰው ሁሉ መጽደቅ ስለሚፈልግ የተመሠረቱትን ሥርዓቶችና ሕጎች ለመጠበቅ የተቻላቸውን ጥረት ያደርጉ ነበር።

ጳውሎስም ራሱ እንኳ፥ ሥርዓትንና ሕግን በመጠበቅ ሊጸድቁ ከሞከሩ አይሁድ መካከል አንዱ እንደ ነበር መጽሐፍ ቅዱስ ላይ ተጽፏል። ጳውሎስ ከነበረው ከፍተኛ ቅናት የተነሳ፥ ክርስቲያኖችን እስከማሳደድ ደርሶም ነበር። አንድ ቀን ግን ጌታ አይኖቹን አበራለትና ዕውነትን አየው።



ወገኖች፥ ምናልባት ዛሬ እኛም፥ ሕግን ተመክተን፥ በራሳችን የጽድቅ ሥራ የምንመጻደቅና ሌሎች ወገኖችን የምናንቋሽሽ ወይም በሌሎች ላይ የምንፈርድ ከሆነ፥ የዕውነትን መንገድ ከመሳት አልፈን፥ ክርስቶስን ማሳደድ ሊሆንብን ስለሚችል፥ ጌታ ማስተዋል እንዲያበዛልን ወደ ጸጋው መመልከት ያስፈልገናል።

ዶክተር ባርንሃውስ የተሰኙ አገልጋይ፥ ለአንድ ሰው ስለጌታ መመስከር ሲጀምሩ፥ የሚመሰክሩለት ሰው ፥ "እግዚአብሔር ምን እንዳደርግ ነው የሚፈልገው? እርሱ ከእኔ ምን ይፈልጋል? የሚል ጥያቄ አቀረበላቸው። ዶክተር ባርንሃውስም ጥያቄውን ሲመልሱ፥ "እግዚአብሔር የሚፈልገው መታመን ነው!" በማለት ሰው ለመዳን የሚጠበቅበት ብቸኛ ነገር <u>ማመን</u> እንደሆነ አስገነዘቡት።

እግዚአብሔር በእርግጥ የሚፈልገው መታመንን (እንድናምነው)ነው(ዮሐንስ 5፥24)። እንዲሁ በጸጋው ያዘጋጀውን ደኅንነት እንድንቀበል የሚፈልገው በእምነት ነው። ስለዚህ ጳውሎስ፥ ጌታ ኢየሱስ ተገልጦለት አይኖቹን ካበራለት በኋላ፥ የተገነዘበውን ትክክለኛ የጽድቅ መንገድ፥ ሌሎችም እንዲገነዘቡና አምነው እንዲድኑ፥ ጽድቅ በእምነት መሆኑን አሳሰበ።

በሮሜ 4፥1 ላይ፥ ምናልባት አንዳንድ አይሁድ፥ ጳውሎስ ከምዕራፍ አንድ ጀምሮ ሲያቀርብ የነበረውን አሳብ ለመቃወም ወይም ለማፍረስ እንደ ማስረጃ ሊጠቅሱ የሚችሉትን ታሪክ፥ እንዲያውም አስተምሕሮን የሚያጠናክርበት ማስረጃ አድርጎ አቀርቦታል።

1. በሮሜ 4፥1 መሠረት አይሁድ በጳውሎስ አስተምሕሮ ላይ ያላቸውን ተቃውሞ ለማጠናከር እንደማስረጃ ሊያቀርቡ የሚችሉት ታሪክ የማንን ታሪክ ነው? ይህ ታሪክ የጳውሎስ አስተምሕሮ ትክክል አለመሆን የሚያረጋግጥ ማስረጃ አድርገው ሊጠቀሙ የሚችሉት እንዴት ነው?

________________________________________
________________________________________
________________________________________
________________________________________

ሮሜ 4፥1 ላይ ያለው አሳብ፥ አይሁድ የጳውሎስን አስተምሕሮ ለማፍረስ የሚጠቅሱት ታሪክ የአብርሃምን ታሪክ ሊሆን እንደሚችል ያመለክታል።

ምናልባት፥ የጳውሎስን መልዕክት የሚያነቡ አይሁድ፥ "ሕግና ነቢያት አረጋግጠውታል የተባለው ነገር ከአብርሃም ታሪክ ጋር እንዴት ይሄዳል? አባታችን አብርሃምም ይህንን ያረጋግጣል እንዴ? እርሱ እግዚአብሔርን ታዞ በመውጣቱ አይደል የተባረከው? ብለው ሊጠይቁ ይችላሉ።

አይሁድ፥ አብርሃም የተባረከው በፈጸመው ተግባር ማለትም፥ የእግዚአብሔርን ቃል ሰምቶ በመታዘዙ እንደሆነ  አበክረው ያምናሉ።

ስለዚህ ጳውሎስ፥ አብርሃም የጸደቀው በመታዘዙና በፈጸማቸው መልካም ተግባራት ከሆነ በእርግጥ የሚመካበት ነገር ሊኖረው ይችል ነበር። ነገር ግን ቀደም ሲል በምዕራፍ ሦስት ላይ እንደገለጸው፥ ሰው ሁሉ የሚመካበት ነገር የለውም። ይህ ዕውነት አብርሃምንም የሚያካትት እንደሆነ ሲገለጽ፥ "በእግዚአብሔር ዘንድ አይደለም" ይላል።

2. ጳውሎስ የአብርሃምን መጽደቅ ምክንያት በሚገልጽበት ጊዜ፥ ሕግን "በእግዚአብሔር ዘንድ አይደለም።" ሲል ምን ማለቱ ነው? በሮሜ 4፥2-3 መሠረት ጳውሎስ ላቀረበው የመከላከያ አሳብ የሚያቀርበው ማስረጃ ምንድን ነው?

እግዚአብሔር በኃጢአት የተበከለ ሰው በሚያከናውናቸው ውጫዊ ተግባራት አይረካም። ስለዚህ አብርሃምም በፈጸመው መልካም ሥራ ወይም መታዘዝ ምክንያት እግዚአብሔርን ሊያረካ እንደማይችል ጳውሎስ አስታውቋል። ይህንን ዕውነት ደግሞ እግዚአብሔር በቃሉ እንደሚያረጋግጥ አስረድቷል።

3. የእግዚአብሔር ቃል ስለ አብርሃም ምን እንደሚል ነው ጳውሎስ የሚያስታውቀው?

## የእግዚአብሔር ቃል የሚናገረው፥ አብርሃም የጸደቀው በእምነት እንደሆነ ነው

አብርሃም ከእግዚአብሔር ዘንድ በረከት ያገኘበት ምክንያት አይሁድ እንደሚመስላቸው በፈጸመው መልካም ሥራ ሳይሆን፥ በማመኑ እንደሆነ ጳውሎስ በዚህ ክፍል አስገንዝቧል። ይህ አሳብ በእግዚአብሔር ቃል በግልጽ የሰፈረ ቢሆንም አይሁድ ግን አፈ ታሪክን ተከትለው ወይም ቃሉን ሳያስተውሉ በመሰላቸው ሲነዱ ቆይተዋል። ስለዚህ ጳውሎስ ወደ እግዚአብሔር ቃል እንዲመለከቱ አሳስቦ፥ በቃሉ የተገለጠውን ዕውነት አብራርቷል።

አንድ ጊዜ፥ አንድ ወንድም ወደሚያውቃቸው ወገኖች እየደወለ፥ "ፈውስ ለእግዚአብሔር ልጆች እንደ እንጀራ ነው።" የሚለው ጥቅስ የት ነው የሚገኘው?" በማለት ይጠይቅ ነበር።

ይህ ጥያቄ ለኛም ቢቀርብ ምን አልባት፥ "ዘፍጥረት ወይም ዘጸአት ወይም ደግሞ ራዕይ ላይ



ነው።" ብለን ለመናገር ይቃጣን ይሆናል፥ ምክንያቱም ሲባል ሰምተን በርግጥ እንዲህ የሚል ጥቅስ እንዳለ ይመስለናል።
ነገር ግን የእግዚአብሔር ቃል በርግጥ እንደዚያ ይላል? አይደለም። ነገሩ በማቴዎስ 15 ላይ የተጠቀሰችው ከነናዊት ሴት፥ ጌታ ኢየሱስ ልጇን እንዲፈውስላት ስትማጸን ጌታ ኢየሱስ፥ "የልጆችን እንጀራ ይዞ ለቡችሎች መጣል አይገባም" ብሎ የተናገረውን ተመርኩዞ የተቃኘና እየተለመደ መጥቶ ራሱን የቻለ ጥቅስ የሆነ አባባል ሳይሆን አይቀርም።

ምንም እንኳ አባባሉ ከመጽሐፍ ቅዱስ አሳብ ብዙ የራቀ ባይሆንም፥ ከቃሉ የራቁ አስተምሕሮዎች በመካከላችን የሚሰርጹትና እንደ ውሃ እያሳሳቁ የሚወስዱት በእንደዚህ ያለ መልኩ ነው። ስለዚህ የእግዚአብሔር ቃል ምን ይላል ብሎ ቃሉን በግል ማወቅና መገንዘብ አስፈላጊ ነው። የሚማርክ ተናጋሪን ሙሉ ለሙሉ አምኖ በጭፍን ከመከተልም፥ ሌሎች የእግዚአብሔር ሰዎች ደግሞ በተባለው ጉዳይ ላይ የሚሉትን የእግዚአብሔርን ቃል በማስደገፍ መረዳት ይጠቅማል።

4. በሮሜ 4፥3፥ "አብርሃምም እግዚአብሔርን አመነ ጽድቅም ሆኖ ተቈጠረለት።" ይላል። በዚህ ክፍል "አመነ" ሲልና "ጸደቀ" ሲል ምን ለማለት ፈልጎ ነው? (እምነት ማለትና ጽድቅ ማለት ምን ማለት ነው?)

- እምነት ማለት ባመኑት ላይ ሙሉ ለሙሉ ተደግፎ ማረፍና መረጋጋት ሲሆን፥ እውነተኛ እምነት የሕይወትን አቅጣጫ ባመኑት ጉዳይ መሠረት እንዲቃኝ ያደርጋል።

  እምነት 'ቼክ' ተቀብሎ በአካውንት ውስጥ እንደ ማስገባት ነው። የእምነት 'ቼክ' ተስፋ ሲሆን አካውንታችን ውስጥ ካስገባን በኋላ በቼኩ ላይ የተጻፈውን ቁጥር ያህል ገንዘብ እንዳለን እርግጠኛ መሆንና ከገንዘቡ ውስጥ አውጥቶ ለመጠቀም እርምጃ መውሰድ እምነት ነው።

  እግዚአብሔር መልካም ሊያደርግ የሚችለው ወይም የሚወድደው ለሚያምን ነው። (ዘፍጥረት 15፥6-7፣ ሮሜ 4፥13፣የሐዋርያት ሥራ 16፥31፣ ሮሜ 1፥16፣ 3፥21-22፣ ዮሐንስ 3፥36፣ ኤፌሶን 1፥18-19፣ ሮሜ 15፥13፣ ማርቆስ 16፥16-17፣)

- ጽድቅ በሕግ ፊት ቀርቦ ከፍርድ ነጻ መሆንን የሚያመለክት ቃል ሲሆን፥ ከደኅንነት አኳያ፥ እኛም በእግዚአብሔር ፊት ከበደላችን እዳ ነጻ ወጥተን፥ በእግዚአብሔር ፊት ተቀባይነት ያለን (ትክክለኛ መስመር ላይ ያለን) ተደርገን መቆጠራችንን የሚገልጽ ቃል ነው።

“የአብርሃም ጽድቅ ወይም በረከት ማግኘት፥ የመታዘዙ ወይም የመልካም ሥራው ውጤት ነው።” የሚለውን አመለካከት ለመከላከል፥ ጳውሎስ የተጠቀመው ቃል፥ “ተቆጠረለት” የሚል ነው።

5. ይህ፥ “ተቆጠረለት” የሚለው ቃል የአብርሃም ጽድቅ የሥራው ውጤት አለመሆኑን የሚያረጋግጠው እንዴት ነው?

ተቆጠረለት የሚለው ቃል የአብርሃም ጽድቅ እንዲሁ ተጨምሮለት መሆኑን የሚገልጽ ስለሆነ ጽድቁ የሥራው ውጤት እንዳልሆነ ያረጋግጣል።

አብርሃም ጽድቅ ያገኘው በመታዘዙ ቢሆን ኖሮ፥ “አብርሃም የሚገባውን ደሞዝ ተቀበለ ።” እንጂ ተቆጠረለት እንደማይባል በመጠቆም ነው ጳውሎስ ያቀረበውን ማስረጃ ያብራራው።

6. በሮሜ 4፥4 ፥ “ለሚሠራ ደመወዝ እንደ ዕዳ ነው እንጂ እንደ ጸጋ አይቈጠርለትም” በማለት ሲናገር ምን ማለቱ ነው? በተለይ “እንደ ዕዳ” ሲል ምን ለማለት ፈልጎ ነው?

የአብርሃም ጽድቅ የሥራው ውጤት ቢሆን ኖር ለእግዚአብሔር እንደ ዕዳ ይሆን ነበር። ስለዚህ እግዚአብሔር ሊቀበል የሚገባውን ምሥጋና ያጓድላል።

ወገኖች፥ ምናልባት በራሳችን የጽድቅ ሥራ የምንመካ ከሆነ፥ በ2ኛ ቆሮንቶስ 10፥17-18፥ ” ... እግዚአብሔር የሚያመሰግነው እንጂ ራሱን የሚያመሰግን እርሱ ተፈትኖ የሚወጣ አይደለምና። ስለሚል ትምክህታችን ማን ላይ እንዳለ መፈተን አስፈላጊ ነው።

7. በሮሜ 4፥5 ጳውሎስ ምን ይላል? ምንስ ለማለት የፈለገ ይመስልዎታል?



በሮሜ 4፥5 ላይ፥ “ነገር ግን ለማይሠራ፥ ኃጢአተኛውንም በሚያደድቅ ለሚያምን ሰው እምነቱ ጽድቅ ሆኖ ይቆጠርለታል።” ይላል። ይህንን ሲል ጽድቅ የሚገኘው ሕግን በመጠበቅ ሳይሆን በጸጋው ነው ብለው በጸጋው የሚታመኑ ሰዎችን እግዚአብሔር እንደሚያጸድቅ ለመግለጽ ነው።

ጽድቅ ኃጢአትን ይቅር ብሎ ኃጢአተኛውን “ጻድቅ” ከሚለው ከእግዚአብሔር እንጂ፥ ከሰው ብቃትና ጥረት የሚገኝ አይደለም። ጳውሎስ በማስረጃ አጠናክሮ ሊያስገነዝብ የሞከረው ይህንን ዕውነት ነው። ስለዚህ፥ “የሚመካ በእግዚአብሔር ይመካ ተብሎ እንደ ተጻፈው ይሆን ዘንድ፥ ከእግዚአብሔር ዘንድ ጥበብና ጽድቅ ቅድስናም ቤዛነትም በተደረገልን በክርስቶስ ኢየሱስ የሆናችሁ ከእርሱ ነው።”

8. ከዛሬው ጥናት ምን ተገነዘቡ?

# ክፍል አስራ አራት

## ጽድቅ በእምነት - የደኅንነት መስፈርት
## የአብርሃም ምሳሌነት (4፥6-25)

እንደዚህ ዳዊት ደግሞ እግዚአብሔር ያለ ሥራ ጽድቅን ስለሚቆጥርለት ስለ ሰው ብፅዕና ይናገራል እንዲህ ሲል፡- ዓመፃቸው የተሰረየላቸው ኃጢአታቸውም የተከደነላቸው ብፁዓን ናቸው፤ ጌታ ኃጢአቱን የማይቆጥርበት ሰው ብፁዕ ነው። እንግዲህ ይህ ብፅዕና ስለ መገረዝ ተነገረ? ወይስ ደግሞ ስለ አለመገረዝ? እምነቱ ለአብርሃም ጽድቅ ሆኖ ተቆጠረለት እንላለንና። እንዴት ተቆጠረለት? ተገርዞ ሳለ ነውን? ወይስ ሳይገረዝ? ተገርዞስ አይደለም፥ ሳይገረዝ ነበር እንጂ። ሳይገረዝም በነበረው እምነት ያገኘው የጽድቅ ማኅተም የሆነ የመገረዝን ምልክት ተቀበለ፤ ይህም እነርሱ ደግሞ ጻድቃን ሆነው ይቆጠሩ ዘንድ ሳይገረዙ ለሚያምኑ ሁሉ አባት እንዲሆን ነው፥ ለተገረዙትም አባት እንዲሆን ነው፤ ይኸውም ለተገረዙት ብቻ አይደለም ነገር ግን አባታችን አብርሃም ሳይገረዝ የነበረውን የእምነቱን ፍለጋ ደግሞ ለሚከተሉ ነው። የዓለምም ወራሽ እንዲሆን ለአብርሃምና ለዘሩ የተሰጠው የተስፋ ቃል በእምነት ጽድቅ ነው እንጂ በሕግ አይደለም። ከሕግ የሆኑትስ ወራሾች ከሆኑ እምነት ከንቱ ሆኖአል የተስፋውም ቃል ተሽሮአል፤ ሕጉ መቅሠፍትን ያደርጋልና፤ ነገር ግን ሕግ በሌለበት መተላለፍ የለም። ስለዚህ ከሕግ ብቻ ሳይሆን ከአብርሃም እምነት ደግሞ ለሆነ ለዘሩ ሁሉ የተስፋው ቃል እንዲጸና እንደ ጸጋ ይሆን ዘንድ በእምነት ነው፤ እርሱም፡- ለብዙ አሕዛብ አባት አደረግሁህ ተብሎ እንደ ተጻፈ፥ ለሙታን ሕይወት በሚሰጥ የሌለውንም እንዳለ አድርጎ በሚጠራ ባመነበት በአምላክ ፊት የሁላችን አባት ነው። ዘርህ እንዲሁ ሊሆን ነው እንደ ተባለ፥ ተስፋ ባልሆነው ጊዜ የብዙ አሕዛብ አባት እንዲሆን ተስፋ ይዞ አመነ። የመቶ ዓመትም ሽማግሌ ስለ ሆነ እንደ ምውት የሆነውን የራሱን ሥጋና የሳራ ማኅፀን ምውት መሆኑን በእምነቱ ሳይደክም ተመለከተ፤ ለእግዚአብሔርም ክብር እየሰጠ፥ የሰጠውንም ተስፋ ደግሞ ሊፈጽም እንዲችል አጥብቆ እየተረዳ፥ በእምነት በረታ እንጂ በአለማመን ምክንያት በእግዚአብሔር ተስፋ ቃል አልተጠራጠረም። ስለዚህ ደግሞ ጽድቅ ሆኖ ተቆጠረለት። ነገር ግን። ተቈጠረለት የሚለው ቃል ስለ እርሱ ብቻ የተጻፈ አይደለም፥ ስለ እኛም ነው እንጂ፤ ስለ በደላችን አልፎ የተሰጠውን እኛን ስለ ማጽደቅም የተነሣውን ጌታችንን ኢየሱስን ከሙታን ባስነሣው ለምናምን ለእኛ ይቈጠርልን ዘንድ አለው።



ጳውሎስ፥ "ጽድቅ በእምነት" መሆኑን ለማረጋገጥ፥ አብርሃም የጸደቀው በእምነት መሆኑን እንደ ማስረጃ ካቀረበ በኋላ፥ አስተምሕሮውን የበለጠ አጠናክሮ ለማቅረብ፥ በአይሁድ ዘንድ ከፍተኛ ቦታ ያለውን ዳዊትን ይጠቅሳል። ዳዊት በዚህ ክፍል የተናገረው፥ "እግዚአብሔር ያለ ሥራ ጽድቅን ስለሚቆጥርለት ስለ ሰው ብፅዕና።" እንደ ሆነ ጳውሎስ ገልጿል።

1. ብፅዕና ማለት ምን ማለት ነው?

---

በአዲሱ መደበኛ ትርጉም መጽሐፍ ቅዱስ ላይ ብፅዕና የሚለውን፥ 'esher' የሚለውን የዕብራይስጥ ቃል ተከትሎ ፥ ደስ መሰኘት በሚል ተክቶታል። የእግሊዝኛው NIV መጽሐፍ ቅዱስ ደግም ብፁዕ የሚለውን Blessed (የተባረከ) ይለዋል። ስለዚህ፥ በጥቅሉ ስንገልጸው ግን፥ ብፅዕና ከደስታና ከበረከት መጥለቅለቅ በተጨማሪ "ብቁ" መሆንንም ያመለክታል።

2. በጳውሎስ አባባል፥ ዳዊት፥ "ብፁዕ ነው" የሚለው ሰው ምን አይነትን ሰው ነው?

---

ኃጢአቱ ይቅር ያልተባለለት ሰው ብፁዕ አይደለም። ማለትም፥ የበደሉ ቀንበር በላዩ ተቀምጦ ስለሚያስጨንቀው እውነተኛ ደስታ ሊኖረው አይችልም። ምክንያቱም በጌታ ፊት ሊያቆመው የሚችል ብቃት የለውም። ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት የሌለው በፍርሃትና መሸማቀቅ ማጥ ስለተዘፈቀ፥ ነፍሱ በደስታ ልትፍለቀለቅ ፈጽሞ አትችልም። ስለዚህ ከአዳም ጀምሮ ያለው የሰው ዘር ሁሉ፥ ከውድቀት በኋላ በሐፍረት፥ በፍርሃትና በጭንቀት ውስጥ መኖር ግድ ሆኖበታል።

ጻድቅ የሆነው እግዚአብሔር በሰው ኃጢአት አዝኖ ስለነበርና፥ እግዚአብሔር ትዕዛዙ በመጣሱ ተቆጥቶ ስለነበር፥ በሰውና በእግዚአብሔር መካከል የመረረ ጠብ ሆኗል። ስለዚህ ኃጢአተኛ የሆነው ሰው ወደ ቀድሞው ለመመለስ የሚያደርጋቸው ተግባራት ሁሉ በቂ አይደሉም። ሰው በሚያቀርባቸው መስዋዕት እግዚአብሔርን ማርካት ወይም ደስ ማሰኘት አይችልም (1ኛ ሳሙኤል 15፥22) ።

ዳዊት በመዝሙር 32፥1-2 ያስተላለፈው አሳብ፥ ከራሱ ልምድ ባየውና በመንፈስ አርቆ በተመለከተው መሠረት ነበር። ምክንያቱም፥ ዳዊት ራሱ በኃጢአት ወድቆ

የእግዚአብሔርን ቅድስና ማርካት ፈጽሞ በማይችልበት ሁኔታ ውስጥ በነበረበት ጊዜ፥ በንስሐ እግዚአብሔር እግር ሥር ሲወድቅ፥ ምሕረትን አግኝቶ እንደተነሳ 2ኛ ሳሙኤል 12፥13 ላይ ተገልጿል።

ስለዚህ ዳዊት፦ እግዚአብሔር ያለ ልፋት (የሰው ልፋት ሳይጨመርበት እንዲሁ በራሱ) ኃጢአትን ይቅር እንደሚልና ይቅር ያለውን ኃጢአት በታሪክ መዝገብ ውስጥ አስፍሮ እንደማያስቀምጠው በመዝሙር 32፥1-2 ላይ አስገንዝቧል።

ሐዋርያው ጳውሎስ ይህንንን የዳዊትን ትምሕርት(መዝሙር) እንደ ማስረጃ በማቅረብ፥ እግዚአብሔር በልጁ በክርስቶስ በኩል ያዘጋጀው ጽድቅ ከሰው ተግባር ጋር የማይገናኝ ነጻ ስጦታ መሆኑን አረጋግጧል።

ወገኖች፥ ከጭንቀት፣ ከፍርሃትና ከሥጋት ውስጥ ወጥተን፥ በእግዚአብሔር የደስታ በረከት ለመጥለቅለቅ፥ እግዚአብሔርን ማመን ያስፈልጋል።

ብቃታችን ከእግዚአብሔር በመሆኑ፥ ትምክህታችን የራሳችን የጽድቅ ሥራ ሳይሆን፥ ስለ እኛ ቤዛ ሆኖ በመስቀል በኩል እዳችን በከፈለው በጌታ በክርስቶስ ኢየሱስ ብቻ ነው።

3. በሮሜ 4፥9-10 ጳውሎስ የመከላከያ ሐሳቡን እንዴት ነው የሚያቀርበው? የአብርሃም ብፅዕና ወይም ብቃት ከመገረዙ ጋር የተያያዘ ነው? ለምን?

---

---

---

---

በሮሜ 4፥9 ጳውሎስ የመከላከያ ሐሳቡን አጠናክሮ የሚያቀርበው ስለ አብርሃም ግዝረት ትንታኔ በመስጠት ነው። በዚህ ክፍል አብርሃም ጽድቅ ሆኖ የተቆጠረለት ከመገረዙ በፊት ስለነበረ መባረኩ የመገረዙ ውጤት እንዳልሆነ ገልጿል።

አብርሃም፥ “ጻድቅ” የተባለው ሎጥን ከግዞት ካስለቀቀ በኋላ፥ እግዚአብሔር የሰጠውን ተስፋ ሲያምን ነው። አብርሃም ሎጥን ሲያስለቅቅ ገና አልተገረዘም ነበር። ከዚያ በኋላ ሰማንያ ስድስት ዓመት ሲሞላው እስማኤል ተወለደ (ዘፍጥረት 16፥16)፥ በዚያን ጊዜም አብርሃም ገና አልተገረዘም ነበር። በኋላም፥ በዘፍጥረት 17 እንደተጠቀሰው፥ በ99 ዓመቱ ተገረዘ።

እንግዲህ አብርሃም፥ “ጻድቅ” በመባሉና በመገረዙ መካከል ያለውን የጊዜ ርቀት ስንመለከት፥ ጽድቅ በሰው መታዘዝና መልካም ሥራ የሚገኝ ሳይሆን፥ እግዚአብሔር በመለኮታዊ ብቃቱና ስልጣኑ ለሰዎች የሚቆጥረው (የሕይወት አካውንት ውስጥ የሚያስገባው) መሆኑን ማረጋገጥ ይቻላል።



በአዲስ ኪዳን ጥምቀት ከግዝረት ጋር ትይዩ ተደርጎ ይጠቀሳል (ቆላስይስ 2፥11-12) ። አይሁድ፥ ግዝረት ያጸድቃል ብለው ያምኑ እንደነበር ዛሬ ደግሞ ጥምቀት በደኅንነት ላይ ቀጥተኛ ሚና አለው የሚሉ ይኖራሉ።

4. ይህንን በተመለከተ እርስዎ ምን ይላሉ? ጥምቀት ደኅንነትን ያመጣል? ክርስቲያኖች የምንጠመቀው ለምንድን ነው? በክርስትና ውስጥ የጥምቀት ትክክለኛ ሚና ምንድን ነው ይላሉ?

---

---

---

---

በዚህ ጉዳይ ላይ በተለይ ሁለት ተቃራኒ አመለካከቶች አሉ፥ እነርሱም፦

- ጥምቀት በደኅንነት ላይ ቀጥተኛ ተጽዕኖ ያመጣል የሚሉና
- ጥምቀት የሚያጸድቅ ሳይሆን የውስጥ መለወጥ ውጫዊ ነጸብራቅ ነው የሚሉ ናቸው።

ክርስቲያኖች የምንጠመቀው ትዕዛዝ ስለሆነ ነው። ያመንነውን እንድንመሰክር ስለሚጠበቅብን፥ ጌታ እንዳዘዘው እምነታችንን በአደባባይ አውጥተን ለመመስከር እንጠመቃለን።

ጥምቀት የውስጥ መለወጥ ውጫዊ ነጸብራቅ ነው። የጥምቀትን አገልግሎት በሦስት ጎራዎች ከፍለን ልናየው እንችላለን፦

I. ምልክት

- ታጥቦ የመንጻት ምልክት ነው
- አዲስ ሆኖ የመወለድ ምልክት ነው

II. መለያ

- አማኝ ከእግዚአብሔር አብ፣ ከእግዚአብሔር ወልድ፣ ከእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ አንድ አምላክ ጋር መተባበሩ የሚለይበት ነው።
- አማኝ ከክርስቶስ ቤተሰብ ጋር መዋኃዱ የሚለይበት ነው

III. አዋጅ

- በክርስቶስ ኢየሱስ አዲሱን ማንነት መያዙን የሚያውጅበት ነው

በሮሜ 4፥11 ጳውሎስ፥ ጽድቅ በእምነት መሆኑን በማስረጃ ሲያቀርብና ሲያብራራ፥ ስለ ግዝረት ሚና ባጭሩ ጠቅሶ አልፏል። በዚህ ክፍል ጳውሎስ መገረዝ እንደ ምልክት መሆኑን አስገንዝቧል።

በጋብቻ ጊዜ ቀለበት የሚታሰረው፥ ጥንዶቹ በጋብቻ መተሳሰራቸውን ለማመልከት ነው እንጂ ቀለበቱ የሰዎችን ትዳር የሚያጸድቅ ሆኖ አይደለም።

በተመሳሳይ፥ ጳውሎስ እንደገለጸው፥ የአብርሃም መገረዝ የመጽደቁና የመለየቱ ምልክት እንጂ የጽድቁ ማረጋገጫ ወይም ምክንያት አይደለም።

ዛሬ በተለያዩ ምክንያቶች በእጃቸው ላይ ቀለበት ማድረግ ያልቻሉ ባለ ትዳሮች ይኖራሉ። እነዚህ ሰዎች ጋብቻቸው በሕግ የጸደቀ በመሆኑ ቀለበት አለማድረጋቸው የጋብቻቸውን ትክክለኛነት አጠያያቂ ሊያደርገው አይችልም።

እንደዚሁም በሮሜ 4፥11፥ "እነርሱ ደግሞ ጻድቃን ሆነው ይቆጠሩ ዘንድ ሳይገረዙ ለሚያምኑ ሁሉ አባት እንዲሆን ነው።" እንደሚል፥ ጽድቅ የሚገኘው በእምነት እንጂ በመገረዝ አይደለም። አለመገረዝ ጽድቅ ማግኘትን አጠያያቂ ሊያደርገው አይችልም። ምክንያቱም ለሚያምን ሰው እግዚአብሔር እምነቱን ጽድቅ አርጎ ይቆጥርለታልና ነው።

5. በአዲስ ኪዳን የመጽደቅ ማኅተም ምንድን ነው?

---

## መንፈስ ቅዱስ (ኤፌሶን 1፥13) ፤

በአዲስ ኪዳን ግዝረት ከጥምቀት ጋር ትይዩ ሚና ቢኖረውም እንኳ፥ ከጥምቀትም በፊት ከመዳናችን ጋር ተያይዞ በውስጠኛው ሰውነታችን ውስጥ የሚደረግ መንፈሳዊ ሥርዓት እንደሆነ ተጠቅሷል (ቆላስይስ2፥10-12) ። ስለዚህ በአዲስ ኪዳን ግዝረት ስንል፥ አሮጌው ማንነታችን ሞቶ አዲስ ሆነን መነሳታችንን ለማመልከት ነው።

6. በሮሜ 4፥12 ላይ ጳውሎስ፥ "የእምነቱን ፍለጋ ደግሞ ለሚከተሉ ..."ሲል ምን ማለቱ ነው?

---



## ይህ ቃል የአብርሃምን የእምነት ፈለግ ወይም ዱካውን በመከተል በእምነት ጌታ ፊት የቀረቡ ጽድቅን ያገኛሉ ማለቱ ነው።

በሮሜ 4፥ 13 ጳውሎስ የጀመረውን አሳብ አጠናክሮ ሲያቀርብ፥ "የዓለምም ወራሽ እንዲሆን ለአብርሃምና ለዘሩ የተሰጠው የተስፋ ቃል በእምነት ጽድቅ ነው እንጂ በሕግ አይደለም።" ይላል። በዚህ ክፍል ላይ፥ "ለዘሩ" የሚለው በሥጋ አይሁድ የሆኑትን ብቻ ሳይሆን በክርስቶስ የአብርሃም የዘር ግንድ ውስጥ የተካተቱትንም ጨምሮ ነው።

ምክንያቱም፥ በዘፍጥረት 18፥18 ለአብርሃም የተሰጠው የበረከት የተስፋ ቃል የአሕዛብንም መባረክ ያካተተ ነበር። የአሕዛብ በረከት ደግሞ በክርስቶስ ኢየሱስ በማመን የሚገኝ ነው። ይህ ባይሆን ኖሮ፥ ጳውሎስ በሮሜ 4፥14 እንደሚናገረው፥ "ከሕግ የሆኑትስ ወራሾች ከሆኑ እምነት ከንቱ ሆኖአል የተስፋውም ቃል ተሽሮአል።" ይባል ነበር።

ይህ ብቻ አይደለም፥ በቁጥር 15 እንደተጠቀሰው መጽደቅ በእምነት ቢሆን ኖሮ አሕዛብ ብቻ ሳይሆኑ፥ አይሁድም እንኳ ተስፋቸው ከንቱ ይሆን ነበር። ምክንያቱም ሕግ ጥፋትን የሚያሳይ እንጂ ብቃት የሚሆን ስላይደለና ማንም ሰው ሕግን ሁሉ ሊፈጽም ስለማይችል፥ ሕግ ለሁሉም ሰው መቅሰፍት ይሆን ነበር።

በሮሜ 4፥16-17 ደግሞ የመጽደቃችን ተስፋ የተመሰረተው፥ የሌለን ወደ መኖር መጥራት በሚችል አምላክ ላይ ስለሆነ፥ አስተማማኝ ተስፋ እንዳለን ያረጋግጣል።

ስለዚህ ጳውሎስ እንደሚገልጸው፥ እግዚአብሔር በመለኮታዊ ሥልጣኑ የኃጢአተኛው አካውንት ውስጥ ጽድቅ እንዲኖር ማድረግ ይችላል። ይህም በክርስቶስ ሆኗል። ዛሬም እኛ ለመጽደቅ የሚጠበቅብን እንደ አብርሃም ሊያጸድቀን በሚችለው ፈጣሪ ማመን ብቻ ነው።

በሮሜ 4፥18-22 እንደተጠቀሰው፥ አብርሃም በራሱ ተስፋ የሚያደርገው ነገር በሌለ ጊዜ፥ ጌታ የተናገረውን አምኖ እንደበረታ፥ በራሳችን ምንም ማድረግ የማንችል ስለሆንን፥ ዝም ብለን የተሰጠንን የተስፋ ቃል በእምነት እንጨብጥ።

አንዳንድ ጊዜ የራሳችን ሁኔታ በራሳችን ላይ ተስፋ እንድንቆርጥ ሊያደርገን ይችላል። ወገኖች፥ ያዳነን፥ ያጸደቀን ጌታ ነው፥ ብቃታችንም እርሱ ጌታ ነው። ስለዚህ ጌታን እየተመለከትን በእምነታችን እንበርታ።

7. በሮሜ 4፥23-25 ጳውሎስ ምን ይናገራል? ምንስ ማለቱ ነው?

---

የአብርሃም ታሪክ ለኛም ትምሕርት ሊሆንልን የሚገባ እንደሆነ ነው ጳውሎስ በዚህ ክፍል የሚገልጸው። ምክንያቱም በአብርሃም ሕይወት የተከናወነው ለኛም የሚሆን ነውና።

የእኛ የክርስቲያኖች ከኃጢአት መንጻት፥ በምንከፍለው መስዋዕት ወይም በምናቀርበው መልካም ሥራ ሳይሆን፥ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ባፈሰሰው ደም ነው።

ክርስቶስ ኢየሱስ ለበደላችን ስርየት ላንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ደሙን አፍስሶአል። በእርሱ ያመንን ሁሉ አሁን ነጻ ነን። በኛ በኩል ከማመን በቀር ለነጻነታችን የምናዋጣው ምንም ነገር የለም!

8. ከዛሬው ጥናት ምን ተገነዘቡ?

______________________________

______________________________

______________________________

______________________________



# ክፍል አስራ አምስት

ነጻነት- የደኅንነት ውጤት
ከቁጣ ነጻ (ሮሜ 5፥1-11)

እንግዲህ በእምነት ከጸደቅን በእግዚአብሔር ዘንድ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ሰላምን እንያዝ፤ በእርሱም ደግሞ ወደ ቆምንበት ወደዚህ ጸጋ በእምነት መግባትን አግኝተናል፤ በእግዚአብሔር ክብርም ተስፋ እንመካለን። ይህም ብቻ አይደለም፥ ነገር ግን መከራ ትዕግሥትን እንዲያደርግ፥ ትዕግሥትም ፈተናን ፈተናም ተስፋን እንዲያደርግ እያወቅን፥ በመከራችን ደግሞ እንመካለን፤ በተሰጠንም በመንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔር ፍቅር በልባችን ስለ ፈሰሰ ተስፋ አያሳፍርም። ገና ደካሞች ሳለን ክርስቶስ ዘመኑ ሲደርስ ስለ ኃጢአተኞች ሞቶአልና። ስለ ጻድቅ የሚሞት በጭንቅ ይገኛልና፤ ስለ ቸር ሰው ግን ሊሞት እንኳ የሚደፍር ምናልባት ይገኝ ይሆናል። ነገር ግን ገና ኃጢአተኞች ሳለን ክርስቶስ ስለ እኛ ሞቶአልና እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን የራሱን ፍቅር ያስረዳል። ይልቁንስ እንግዲህ አሁን በደሙ ከጸደቅን በእርሱ ከቍጣው እንድናለን። ጠላቶች ሳለን ከእግዚአብሔር ጋር በልጁ ሞት ከታረቅን፥ ይልቁንም ከታረቅን በኋላ በሕይወቱ እንድናለን፤ ይህም ብቻ አይደለም፥ ነገር ግን አሁን መታረቁን ባገኘንበት በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በእግዚአብሔር ደግሞ እንመካለን።

በሮሜ 5፥1፥ “እንግዲህ” የሚለው ቃል፥ ጳውሎስ ቀደም ሲል በአራቱ ምዕራፎች ወዳቀረባው አሳብ የሚጠቁምና ወደ ውጤቱ የሚያንደረድር ቃል ነው። ቀደም ባለቱ ምዕራፎች ውስጥ፥ መጀመሪያ ሁሉ ሰው ኃጢአተኛ ስለሆነ ከእግዚአብሔር ቁጣ ሥር መሆኑ ተገልጿል፣ ከዚያም ሰው በራሱ አቅም ወይም ተግባር መጽደቅ እንደማይችል ተገልጿል፣ ቀጥሎም፥ ሰው ሁሉ ሊጸድቅ የሚችልበት መንገድ እምነት እንደሆነ ተገልጿል፣ በሮሜ አምስት ላይ ደግሞ፥ ጻድቅ የመባል ውጤት ምን እንደሆነ መግለጽ ይጀምራል።

1. በሮሜ 5፥1 እንደተገለጸው፥ ባለፉት አራት ምዕራፎች የቀረበው ዕውነት ውጤት ምንድን ነው?

______________________________

______________________________

______________________________

______________________________

ከእግዚአብሔር ጋር ሰላምን መያዝ ነው። ሰው ከኃጢአቱ የተነሳ ከእግዚአብሔር ጋር ተጣልቶ ነበር። ነገር ግን ጌታችን ኢየሱስ ይህንን የጥል ግድግዳ አፍርሶ የእርቅን መንገድ ከፈተ።

> “እርሱ ሰላማችን ነውና፤ ሁለቱን ያዋሐደ በአዋጅ የተነገሩትንም የትእዛዛትን ሕግ ሽሮ በመካከል ያለውን የጥል ግድግዳን በሥጋው ያፈረሰ፤ ይህም ከሁለታቸው አንድን አዲስን ሰው በራሱ ይፈጥር ዘንድ ሰላምንም ያደርግ ዘንድ።” ኤፌሶን 2፥14-15

ባለመታዘዝ ምክንያት ሰው ከእግዚአብሔር ጋር እንደተጣላ መጽሐፍ ቅዱስ ይገልጻል። ስለዚህ በሰውና በእግዚአብሔር መካከል ጠላትነት ተፈጠረ (ሮሜ 5፥10)። ነገር ግን፥ ጌታ ኢየሱስ አለመታዘዝን በመታዘዝ ሽሮና ያለመታዘዝን ቅጣት ተቀብሎ የጠቡን ግድግዳ በማፍረስ ሰውን ከአብ ጋር አስታረቀ። ስለዚህ በክርስቶስ ያመነ ይህንን ሰላም መያዝ ይችላል ማለት ነው።

በሮሜ 5፥1፥ “ሰላምን እንያዝ” የሚለው ቃል በአዲሱ ትርጉም፥ “ሰላም አለን” በማለት የተሻለ ግልጽ አድርጎታል። ይህ፥ “ሰላምን እንያዝ” ወይም “ሰላም አለን” የሚለው ቃል ታድያ፥ በሮሜ 5፥2 እንደተገለጸው፥ በክርስቶስ ያመነ ሁሉ ከእግዚአብሔር ጋር በሰላም ኅብረት ማድረግ መቻሉን ያረጋግጣል።

ጳውሎስ እንደሚናገረው፥ ይህ ሰላም በክርስቶስ የተገኘ የጽድቅ ውጤት በመሆኑ አስተማማኝ ነው። ስለዚህ በእምነት ይህንንን ሰላም መያዝ መቻላችን እርግጥ ነው። ይህ ሰላም ደግሞ ጌታ ኢየሱስ እስካለ ድረስ ጸንቶ የሚኖር ሰላም ነው። በሌላ አባባል ዘላለማዊ ሰላም ነው ማለት ነው።

በሮሜ 5፥1 ጳውሎስ፥ “በእምነት ከጸደቅን” ሲል በክፍል አስራ ስድስት ላይ ለመግለጽ እንደሞከርነው፥ ወንጀለኛ ሰው ከወንጀሉ ነጻ እንደሚሆን፥ ከበደል እዳ ነጻ መሆናችንን መግለጹ ነው።

2. በሮሜ 5፥2 ጳውሎስ “ወደ ቆምንበት ወደዚህ ጸጋ” በማለት የሚጠቅሰው ቃል ምንን ያስገነዝበናል?

---

ጳውሎስ፥ “የቆምንበት ጸጋ” ሲል አሁን አማኝ የሚመላለስበትን የሕይወት ደረጃ ማለቱ ነው። ቀድሞ ሙታን ነበርን ስለዚህ ደረጃችን የሞተ ሰው ያለውን አይነት ደረጃ ነበር። አሁን ግን በክርስቶስ በኩል ሕይወት አግኝተን ሕያዋን ሆነናል(ከእግዚአብሔር ጋር የተቋረጠው ግንኙነት ተቀጥሎልን በሰላም መኖር የምንችልበት ምዕራፍ ላይ ተገኝተናል።)



3. ጳውሎስ በሮሜ 5፥ 2 ጻድቅ የመባልን ሌላ ውጤት ይጠቅሳል። ይህ ውጤት ምንድን ነው?

---

በዚህ ክፍል የተጠቀሰው ሌላው ውጤት በእምነት የመግባት ድፍረት ማግኘትን ነው። በክርስቶስ ያመነ ክርስቲያን ሁል ጊዜ በእግዚአብሔር ፊት መቅረብ ይችላል።

በሮሜ 5፥2 “አግኝተናል” ሲል በክርስቶስ ኢየሱስ በኩል የተቀበልነው የእግዚአብሔር አብ ሥራ መሆኑን ለማስገንዘብ ነው። (ኤፌሶን 1፥11)

4. በሮሜ 5፥2-4 በክርስቶስ ጸጋ ላይ የቆሙ አማኞች ሁሉ የሚመኩበት ጉዳይ እንዳለ ይገልጻል እነዚህ ጉዳዮች ምንና ምን ናቸው? በነዚህ ጉዳዮች መመካት የሚገባው ለምንድን ነው?

---

- በእግዚአብሔር ክብሩ ተስፋና
- በመከራ

<u>በእግዚአብሔር ክብሩ ተስፋ</u>

የእግዚአብሔር ክብር በጣም ሰፊ ከመሆኑ የተነሳ በሙላት ገላልጠን ልናየው አንችልም። ሆኖም ግን፥ በሰው መረዳት ደረጃ አኳያ ስለ እግዚአብሔር ክብር ጥቂቱን ስንረዳ ፥ በከፍተኛ አግራሞትና መደነቅ እንጥለቀለቃለን።

(ከእግዚአብሔር ክብር ጋር ተያይዘው የሚጠቀሱትን በጥቂቱ ለመረዳት የሚከተሉትን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ያንብቡ፦ ዘጸአት 16፥10፤ 24፥16፤ 29፥43፤ 40፥34፤ ዘኊልቁ 14፥14፤ 16፥41-45፤ 1ኛ ነገሥት 8፥10-11፤ መዝሙር 113፥4፤ ኢሳይያስ 2፥19)

5. አማኝ በእግዚአብሔር ክብር ተስፋ መመካት የሚገባው ለምን ይመስልዎታል?

---

ምክንያቱም፥ የቤተ ክርስቲያን ሙላት የእግዚአብሔር ክብር መገለጥ ነው። ያለ እግዚአብሔር ክብር ቤተ ክርስቲያን ምንም ዋጋ የላትም። ስለዚህ ትምክህቷ ክርስቶስ ወይም የእግዚአብሔር

ክብር ተስፋ ነው። ይህ ክብር ደግሞ ቀደም ሲል እንደጠቀስነው ካየነው ከሰማነውና ከተለማመድነው ክብር ሁሉ የላቀ ስለሆነ በእርግጥ ያስመካል።

በሮሜ 3፥ 23 እንደተጠቀሰው፥ ሰው ከእግዚአብሔር ክብር ጎድሎ ነበር። ነገር ግን በክርስቶስ ጽድቅ ከወደቀበት ውርደት ተነስቶ ወደዚህ የእግዚአብሔር ክብር ተስፋ እንዲገባ በር ተከፈተና፥ "ወደ እኔ ኑ!"የሚል የእግዚአብሔር ጥሪ ተላለፈለት። ይህ ጥሪ ታዲያ ከጥሪዎች ሁሉ የከበረና መልካምጥሪ ነው! እኛ ዛሬ ለዚህ ጥሪ እሺ ብለን በመታደማችን፥ "... በመጋረጃ በማይከደን ፊት የጌታን ክብር እንደ መስተዋት እያብለጨለጭን መንፈስ ከሚሆን ጌታ እንደሚደረግ ያን መልክ እንመስል ዘንድ ከክብር ወደ ክብር እንለወጣለን።"

<u>በመከራ</u>

በዮሐንስ ወንጌል፥ "በዓለም ሳላችሁ መከራ አለባችሁ።" ተብሎ እንደተጻፈው፥ ክርስቲያኖች መከራ ሊገጥምን ይችላል። ነገር ግን የሚያበረታታንና የሚደግፈን የእግዚአብሔር ጸጋ ስላለንና ለክፉ የሆነውን ለመልካም የሚቀይር ጌታ ከኛ ጋር ስላለ በመከራችንም እንመካለን።

በቁጥር 5-8 ጳውሎስ የአማኝ ትምክህት በእግዚአብሔር ፍቅር ላይ ስለተመሠረተ አስተማማኝ መሆኑን አረጋግጧል። ጳውሎስ የእግዚአብሔርን ፍቅር አስተማማኝነት ሲያረጋግጥ፥ እግዚአብሔር የወደደን ገና ኃጢአተኞች ሳለን እንደሆነ ገልጿል።

እግዚአብሔር ስለኛ ያለውን ነገርና ለኛ ያዘጋጀውን ነገር የሚወስነው ከኛ ማንነት አኳያ ሳይሆን ከራሱ አስተማማኝ ፍቅር አኳያ ስለሆነ የተስፋውን አስተማማኝነት ያረጋግጥልናል።

6. በሮሜ 5፥11 ደግሞ ጳውሎስ ሌላ የሚመካበትን ጉዳይ ይጠቅሳል። ይህ ጉዳይ ምንድን ነው?

7. ከእግዚአብሔር ጋር መታረቃችንን በተመለከተ፥ "በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በእግዚአብሔር" ትምክሕት ሊኖረን የሚገባው ለምንድን ነው?

የመታደጋችንና የመጽደቃችን ዋና ምክንያት ቃል ኪዳኑን ጠባቂ የሆነው እግዚአብሔር ነው። ስለዚህ በእርሱ መመካትና ክብርን ሁሉ ለእርሱ መስጠት ይገባል።



የእግዚአብሔር ባለ ጠግነትና ጥበብ ዕውቀቱም እንዴት ጥልቅ ነው፤ ፍርዱ እንዴት የማይመረመር ነው፥ ለመንገዱም ፍለጋ የለውም። የጌታን ልብ ያወቀው ማን ነው? ወይስ አማካሪው ማን ነበር? ወይስ ብድራቱን ይመልስ ዘንድ ለእርሱ አስቀድሞ የሰጠው ማን ነው? ሁሉ ከእርሱና በእርሱ ለእርሱም ነውና፤ ለእርሱ ለዘላለም ክብር ይሁን፤ አሜን! (ሮሜ 11፥33-36)

8. ከዛሬው ጥናት ምን ተገነዘቡ?

## ክፍል አስራ ስድስት

ነጻነት- የደኅንነት ውጤት
ከቁጣ ነጻ (5፥12-21)

ስለዚህ ምክንያት ኃጢአት በአንድ ሰው ወደ ዓለም ገባ በኃጢአትም ሞት፥ እንደዚሁም ሁሉ ኃጢአትን ስላደረጉ ሞት ለሰው ሁሉ ደረሰ፤ ሕግ እስከ መጣ ድረስ ኃጢአት በዓለም ነበረና ነገር ግን ሕግ በሌለበት ጊዜ ኃጢአት አይቈጠርም፤ ነገር ግን በአዳም መተላለፍ ምሳሌ ኃጢአትን ባልሠሩት ላይ እንኳ፥ ከአዳም ጀምሮ እስከ ሙሴ ድረስ ሞት ነገሠ፤ አዳም ይመጣ ዘንድ ላለው ለእርሱ አምሳሉ ነውና። ነገር ግን ስጦታው እንደ በደሉ መጠን እንደዚያው አይደለም፤ በአንድ ሰው በደል ብዙዎቹ ሞተዋልና፥ ነገር ግን የእግዚአብሔር ጸጋና በአንድ ሰው በኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ የሆነው ስጦታ ከዚያ ይልቅ ለብዙዎች በዛ። አንድ ሰውም ኃጢአትን በማድረጉ እንደ ሆነው መጠን እንደዚያው ስጦታው አይደለም፤ ፍርድ ከአንድ ሰው ለኵነኔ መጥቶአልና፥ ስጦታው ግን በብዙ በደል ለማጽደቅ መጣ። በአንዱም በደል ሞት በአንዱ በኩል ከነገሠ፥ ይልቁን የጸጋን ብዛትና የጽድቅን ስጦታ ብዛት የሚቀበሉ በአንዱ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በሕይወት ይነግሣሉ። እንግዲህ በአንድ በደል ምክንያት ፍርድ ለኵነኔ ወደ ሰው ሁሉ እንደ መጣ፥ እንዲሁም በአንድ ጽድቅ ምክንያት ስጦታው ሕይወትን ለማጽደቅ ወደ ሰው ሁሉ መጣ። በአንዱ ሰው አለመታዘዝ ብዙዎች ኃጢአተኞች እንደ ሆኑ፥ እንዲሁ ደግሞ በአንዱ መታዘዝ ብዙዎች ጻድቃን ይሆናሉ። በደልም እንዲበዛ ሕግ ጭምር ገባ፤ ዳሩ ግን ኃጢአት በበዛበት፥ ኃጢአት በሞት እንደ ነገሠ፥ እንዲሁ ደግሞ ጸጋ ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ የተነሣ በጽድቅ ምክንያት ለዘላለም ሕይወት ይነግሥ ዘንድ፥ ጸጋ ከመጠን ይልቅ በለጠ።

ብዙ ጊዜ ሰዎች በአለም ለሚታዩ ቀውሶችና ችግሮች እግዚአብሔርን ተጠያቂ ያደርጉታል። የተለያዩ ጥፋቶች ሲመለከቱ ወይም ሲገጥሟቸው፥ “እግዚአብሔር ለምን እንደዚህ አደረገ?!” በማለት ይጠይቃሉ።

1. በሮሜ 5፥12 ለዚህ መሠረታዊ ምላሽ ይሰጣል። ይህ ምላሽ ምንድን ነው? በአለማችን ለሚከሰቱ ጥፋቶች መንስኤ ምንድን ነው?



አዳምና ሄዋን ኃጢአትን ስለሰሩ በአዳም ምክንያት ሞት ወደ ሰው ዘር ሁሉ ተላለፈ። ሞት ሲባል ከሥጋዊ ሞትና ከዘላለም ሞት በተጨማሪ ከእግዚአብሔር ጋር መለያየት ነው። ሞት ለሰው ተዘጋጅቶ የነበረው ሕይወት ተቃራኒ ነው። ሰው ሕያው ነፍስ ሆኖ ከእግዚአብሔር ጋር በመልካም ኅብረትና በተድላ እንዲኖር ተደርጎ ነበር። ነገር ግን በኃጢአት ምክንያት ሰው በእግዚአብሔር ስለተተወ ከተዘጋጀለት መልካም ሕይወት ወጥቶ ክፋት አገኘው። እንግዲህ የክፋት በሩ ኃጢአት ነው ማለት ነው።

2. በሮሜ 5፥13-14 “ሕግ እስከ መጣ ድረስ ኃጢአት በዓለም ነበረና ነገር ግን ሕግ በሌለበት ጊዜ ኃጢአት አይቈጠርም።” ይላል። እስኪ ይህንን አሳብ እንዴት እንደተረዱት ይግለጡ።

3. ሕግ እስከመጣ ድረስ ኃጢአት በዓለም ነበረና ነገር ግን ሕግ በሌለ ጊዜ ኃጢአት አይቆጠርም ካለ በሲና ተራራ ላይ ሕግ ከመሰጠቱ በፊት የነበሩ ኃጢአታቸው አይቆጠርምነበር ማለቱ ነው? ለምን? (ለተሻለ ግንዛቤ ቁጥር አስራ አራትን በደንብ ያጢኑ)

ቁጥር 14 በግልጽ እንደሚያመለክተው ከሙሴ በፊት (በሲና ተራራ ሙሴ ሕግ ከመቀበሉ በፊት) የነበሩ ሰዎች የአዳም ዘር በመሆናቸው በውርስ የተቀበሉት ኃጢአት ነበረባቸው።

ጳውሎስ ከቁጥር 14-15 እንደሚያስረዳው በአንድ ሰው አማካኝነት ኃጢአት ወደ ሰው ዘር ሁሉ ተላልፏል። ስለዚህ ለአዳም የመጣው ሞት ለሰው ሁሉ ደረሰበት። አዳም ኃጢአት በሰራ ጊዜ የሰውን ልጅ ሁሉ ወክሏል። ይህ ውክልና ደግሞ ሊመጣ ላለው አምሳል ነው (ቁ. 14)። ውክልናቸው ግን በጣም የሰፋ ልዩነት አለው። አዳም ሰውን የወከለው ለሞት ሲሆን ጌታ ኢየሱስ ግን ለሕይወት ነው። (1ኛ ቆሮንቶስ 15፥45)

ሮሜ 5፥15-17 የመጀመሪያውንና የሁለተኛውን አዳም ውክልና ውጤት ያነጻጽራል።

4. በዚህ ክፍል በንጽጽር የቀረቡ ሦስት ነጥቦች አሉ። እነዚህን ሦስት ነጥቦች ለመዘርዘር ይሞክሩ።

- ሮሜ 5፥15

- ሮሜ 5፥16

- ሮሜ 5፥17

- የአዳም ውክልና ለሰዎች ሞትን ያስከተለ ሲሆን የክርስቶስ ውክልና ግን ለሰዎች የተትረፈረፈ ሕይወት ያስገኛል።
- አዳም ኩነኔንና ፍርድን ያመጣ ሲሆን ጌታ ኢየሱስ ጽድቅን ያመጣ ነው።
- በአዳም በኩል ሞት የነገሰ ሲሆን በጌታ በኢየሱስ በኩል ሕይወት ነገሰ።

የጌታ ኢየሱስ ውክልና በቁጥር 16 ላይ እንደ ተጠቀሰው በአዳም ከመጣው ውክልና በጣም ይበልጣል ምክንያቱም ኃጢአትን የሚያስወግድ ብቻ ሳይሆን በተጨማሪ የተትረፈረፈ ሕይወትን የሚያስገኝ ነው። ይህን አሳብ ሲያጠናክር ጳውሎስ በቁጥር 17፥ "በአንዱም በደል ሞት በአንዱ በኩል ከነገሠ፥ ይልቁን የጸጋን ብዛትና የጽድቅን ስጦታ ብዛት የሚቀበሉ በአንዱ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በሕይወት ይነግሣሉ።" ይላል።

ጳውሎስ የኃጢአትን አለማቀፋዊ ይዘት ካረጋገጠ በኋላ በቁጥር 18-19 ጽድቅ በክርስቶስ የመገኘቱን እርግጠኝነት አሳስቧል።

በዩናይትድ ስቴትስ ፓርላማ አባላት የመጡበትን ክልል ኅብረተሰብ ስለሚወክሉ ፓርላማው በአንድ ሃገር ላይ ጦርነት ለመክፈት ቢወስን እያንዳንዱ የአሜሪካ ዜጋ ውሳኔውን እንዳስተላለፈ ይቆጠራል። አዳም እግዚአብሔርን ባለመታዘዝ ሲወክለንም በእንዲህ ያለ መልኩ ነው ሊባል ይቻላል። ስለዚህ እያንዳንዱ ሰው ሲወለድ ኃጢአትና የኃጢአት እዳ ተሸክሞ ነው የተወለደው። ነገር ግን ጌታ ኢየሱስ ደግሞ እኛን ወክሎ በመታዘዙ ምክንያት ጽድቅ ደግሞ ወደ ሰው ሁሉ መጣ።





5. ታድያ ኃጢአትና የኃጢአት ዕዳ በሰው ሁሉ ላይ ከመወለድ አንስቶ እንዲሁ ከተላለፈ፥ ጽድቅም እንዲሁ በሰው ሁሉ ላይ ከመወለድ አንስቶ ተላልፏል ማለት ነው። ይህ ሲባል ታድያ፥ ከክርስቶስ ውክልና በኋላ ሁሉ ሰው ድኗል ማለት ነው?

በአዳም የተላለፈውን ለመቀበል ሰው መሆናችን ብቻ በቂ ነበር፥ ስለዚህ ሞት የሁላችን እጣ ፋንታ ሆኖ ነበር። በክርስቶስ የመጣውን ግን እንዲሁ በነጻ የተሰጠን ስለሆነ የእምነት እጃችንን ዘርግተን በፈቃደኝነት መቀበል ይጠበቅብናል። ስለዚህ የሚድነው ያመነ ብቻ (እንደገና የተወለደ) እንጂ ሁሉ ሰው አይደለም።

በክርስቶስ ያገኘነው ጽድቅ፥ በእግዚአብሔር ፊት ጻድቃን ተብለን እንድንታይ የሚያደርግ ብቻ ሳይሆን በቅድስና እንድንኖር ብቃትንም ያስጨበጠን ነው።

6. ይህን አሳብ እንዴት ያብራሩታል?

7. በሮሜ 5፥20፥ "በደልም እንዲበዛ ሕግ ጭምር ገባ" ይላል? ጳውሎስ ይህንንን ሲል ምን ለማለት ፈልጎ ነው?

ጳውሎስ በደልም እንዲበዛ ሕግ ጭምር ገባ ሲል፥ ኃጢአት በመብዛቱ ሕግ እንደ መጣና ሕግ ደግሞ በደልን ስለሚገልጥ ወይም እንቅፋት ስለሚሆን ሰው በሕግ እየተደናቀፈ በመውደቁ፥ በደል ጎልቶ መታየቱን ለመግለጽ ነው።

ጳውሎስ በዚህ ክፈል የጀመረውን መልዕክት ሕግ ገባ ብሎ አላቆመም። ምክንያቱም ጳውሎስ ሊያስተላለፍ የፈለገው መልዕክት ቁልፍ አሳብ ያለው በቁጥር 21 ላይ የተገለጸው ነው። በቁጥር 21 ላይ በክርስቶስ ጽድቅ የተገለጠ ጸጋም እንደ ገባ ጳውሎስ አስገንዝቧል። እንዲያም ነገሩን አክሮ "ጸጋ ከመጠን ይልቅ በለጠ" ብሏል። ጳውሎስ እንዲህ ሲል የጸጋውን ብዛት ወይም የተትረፈረፈ መሆን ለማስገንዘብ ነው። እንግዲህ ወገኖች፥ ከመጠን ይልቅ በበለጠው፥ የኛ

ጭማሪ ወይም ማዋጮ በማያስፈልገው በክርስቶስ ጽድቅ በተገለጠው ጸጋ ሙሉ ለሙሉ ተደግፈን ልንመካ ይገባል።

8. ከዛሬው ጥናት ምን ተገነዘቡ? ከዚህ የሮሜ ሁለተኛው የጥናት ክፍል የተማሩት ምንድን ነው?